# ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ክፍል አንድ

## ትውፊትና መጽሐፍ ቅዱስ

ወንድም አክሊል

5-8-2013

በጽሑፉ ላይ አስተያየት ወይም ጥያቄ ቢኖርዎት በቴሌግራም አድራሻዬ ያድርሱኝ፡ https://t.me/aklil1

ለዌብ ሳይት https://ApostolicAnswers.wixsite.com/aklil

ለቴሌግራም ቻናል https://t.me/ApostolicSuccession

ማውጫ


**የእግዚአብሔር መገለጥ (Revelation of God)** ........ 1

**አጠቃላይ መገለጥ(General Revelation)** ........ 2

**ልዩ መገለጥ (Special Revelation)** ........ 2

**ትውፊት(παράδοσις-Tradition)** ........ 3

**ስለ ቅዱስ ትውፊት ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ፡** ........ 6

**ስለ ቅዱስ ትውፊት ማስረጃ ከሃዋርያት በኋላ ከተነሱ አባቶች** ........ 8

**መጽሐፍ ቅዱስ** ........ 15

**ብሉይ ኪዳን** ........ 16

**ሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ(Septuagint, LXX.)** ........ 16

**ማሶሬቲክ ቴክስት(Masoretic Text) እና ሰብዓ ሊቃናት (ልዩነት)** ........ 22

**የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ቀኖና** ........ 27

**ፕሮቴስታንቱ ለማይቀበሏቸው መጽሐፍት ጥንታዊ ማስረጃዎች** ........ 31

**የብሉይ ኪዳን ቀኖና ላይ የሚያነሷቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው፡** ........ 42

**ሐዲስ ኪዳን** ........ 57

ዋቢ መጻሕፍት ........ 59

## የእግዚአብሔር መገለጥ (Revelation of God)

የእግዚአብሔር መገለጥ ስንል ፈጣሪ እራሱን ለፍጥረቱ በተለይም ለሰዎች የገለጠበት መንገድ እያልን ነው። የአንድ ሃይማኖት መሰረቱ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ባልገለጠበት መልኩ እኛ ልናውቀው አንችልምና። እግዚአብሔርን በባህሪው(οὐσία – essence) የሚያውቀው ማንም የለም። በመጽሐፈ ኢዮብ 11:7 ላይ እንዲህ እንደተባለ፡ "የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን?" ሃዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።"(1ቆሮ 2፡11) በማለት እንደተናገረ ማለት ነው። ስለዚህም እግዚአብሔርን የምናውቀው በመገለጡ(ἐνέργεια - energies) ብቻ ነው። ለምሳሌ ጸሐይ ምን ያህል ትሞቃለች ብንል ምናልባት እያንዳንዳችን እንዳለንበት አካባቢ 24°C ፣ 35 °C እያልን እንመልስ ይሆናል። ውኃን በእሳት ስናፈላ መፍላት የሚጀምረው በ100 °C ነው። 100 °C ውኃ የማፍላት ያህል ሙቀት ካለው 1000 °C ወይም ደግሞ በጣም ከፍ አድርገን 100,000 °C ምን ዓይነት ሙቀት ይኖረው ይሆን..?? የጸሐይ ሙቀት ብለን ያነሳነው ጸሐይ እኛ ጋር የደረሰችበት ወይም ደግሞ እንበለውና ራሷን ለእኛ የገለጠችበት የሙቀት መጠን እንጂ ምናልባት ጠጋ ብንላት በሚያስገርም ሁኔታ ሙቀቷ ከ15,ooo,ooo(15 ሚሊዮን) °C በላይ እደሆነ ይነገራል። ያው እኛ ግን የምናውቃት ለእኛ በደረሰችበት ያህል ነው። እንደዚሁ አምላክ እግዚአብሔርም የሚታወቀው እኛ በምንችለው ልክ እራሱን በገለጠው ልክ ነው። ጸሐይ ለእኛ የተገለጠችበትን የሙቀት መጠን ይዘን የጸሐይ ትክክለኛው ሙቀትም ይኼው ነው ብለን እንደማንወስን እንዲሁ ደግሞ እግዚአብሔር እኛ በምንረዳው ልክ ዝቅ ብሎ ሲገለጥልን በዚህ መገለጥ ልንወስነው አንችልም። ይህም ማለት ለእግዚአብሔር የተነገሩ ቃላትን ሁሉ ለባህሪው ሰጥተን ልንናገር አይገባም። ለዛም ነው ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እንዲህ ያለው፡ "ምናልባት አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር የተነገረበት ሰዋዊ አነጋገር(Metaphor) ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ ከሆነ ይህንን ጌታ በተሳሳተ መልኩ በመግልጽ ይስታል።"[1] እግዚአብሔር ደግሞ ራሱን በተለያየ መንገድ የገለጠ ሲሆን በአጠቃላይ ግን መገለጡን ለሁለት ከፍለን ልንመለከት እንችላለን።

[1] St. Ephrem the Syrian: Hymns on Paradise, 11:6 [Dr. sebastean brock]

**<u>አጠቃላይ መገለጥ</u>**<u>(General Revelation)</u>:- ይህ መገለጥ እግዚአብሔር በፈጠረው በሰው እና በሌሎች ፍጥረቱ የሚገለጥበት መንገድ ነው። በዘፍ 1፡26 "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌችን እንፍጠር" ያለ አምላክ በራሱ አምሳል በፈጠረው ሰው ውስጥ ሊገለጥ ይችላል። ለምሳሌ በሰዎች ያለው ህሊና ክፉና ደጉን መለየቱ ይህም በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ የተቀመጠ ሕገ እግዚአብሔር ነው። ሃዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 2፡14-16 እንዲህ ይላል፡ "ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ **በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ** ያሳያሉ።" ስለዚህም በሰዎች ውስጥ የሚኖረው መልካም ነገር ሁሉ የአምላክን መገለጫ የሚያሳይ ነው። ሰው እንዲሁ ማየቱ መስማቱም ምንም እንኳን በሰው መልኩ ባይሆንም እግዚአብሔርንም በባህሪው ሁሉን ማየትና መስማት እንደሚችል ያሳያል። በሌሎቹም ሥነ ፍጥረቱ እንዲሁ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ ነውና በእነዚህ ፍጥረታት እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ የሁሉ ፈጣሪ መሆኑ መታወቂያው ይሆናል። ሰለሞን በጥበቡ "ሥራውንም እያዩ ሰሪውን አላወቁም" (ጥበብ 9፡1) በማለት እንደተናገረ ሰሪው ከሥራውም ይታወቃልና ነው። ይህንን የሰለሞንን ንግግር በመያዝ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ እንዳለ፡ "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና..." (ሮሜ 1፡20) መዝሙረኛውም እንዲህ እንዳለ፡ "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።"(መዝ 19፡1) ይህ መገለጥ ስለ እግዚአብሔር የተወሰነ ያሳውቀን እንጂ ወደ ድኅነት የሚመራ ግን አይደለም።

**<u>ልዩ መገለጥ</u>** <u>(Special Revelation)</u>:- ይህ ወደ ድኅነት የሚመራ መገለጥ ደግሞ እግዚአብሔር ራሱን ለሕዝቡ ቀጥታ በተለያየ መልኩ በሕልም ወይም በመልአክ በኩል በነቢያት በኩል የገለጠበት በኋላም ደግሞ የመጨረሻውና ትልቁ መገለጡን በልጁ ሥጋዌ በኩል ያደረገበት መንገድ ነው። ይህንን ልዩ መገለጥ የምናገኘው ደግሞ በቅዱስ ትውፊት(sacred tradition) እና በመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ለነገረ መለኮትም ዋና ምንጮቻችን እነሱ(መጽሐፍ ቅዱስና ትውፊት) ናቸውና እግዚአብሔር በረዳን ልክ አጠር አድርገን እናያለን።

## **ትውፊት(παράδοσις-Tradition)**

ትውፊት፡ ማለት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ውርስ ሲሆን በሁለት ከፍለን አንዱን ሰዋዊ ትውፊት ሌላውን ደግሞ ቅዱስ ትውፊት ልንለው እንችላለን። ሰዋዊ ትውፊት(ልማድ) የምንለው ከአምላክ መገለጥ ጋር የሚያያዝ ሳይሆን ሰዎች እንደ አካባቢያቸው የሚኖራቸውን ባህል ወይም ልማድ የሚያሳይ ነው። እንደማንኛውም አካባቢ አይሁዳውያንም የራሳቸው ልማድ እንደነበራቸው ግልጽ ነው። ለምሳሌ እጅን ታጥቦ መብላት ሰዋዊ ባህላቸው ነበር። ይህንን ልማዳቸውን ወይም ወጋቸውን ደግሞ ከአምላክ ቃል አስቀድመው ሲይዙትና ጌታ ኢየሱስም ሲወቅሳቸው በመጽሐፍ ቅዱስ እንመለከታለን(ማርቆስ 7)። ሌላኛው ሁለተኛው ትውፊት ደግሞ ቅዱስ(ክርስቲያናዊ) ትውፊት ነው። ይህ ደግሞ ከጌታ ጀምሮ በሐዋርያት በኩል ብሎም በአባቶች አንዱ ትውልድ ለሌላኛው ሲያስተላልፍ የኖረው የእግዚአብሔር አምላክ መገለጥ(Revelation) ነው። ትውፊት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በግሪኩ ቋንቋ ፓራዶሲስ(παράδοσις) የሚል ሲሆን ቀጥታ ትርጉሙም "የትምሕርት ሽግግር(ከአንዱ ወደ ሌላው) ወይም ትውፊት" እንደማለት ነው።[2] "በቃል ወይም በጽሑፍ የተደረገን ነገር ማቀበል ወይም ማስተላለፍ" እንደማለትም ይሆናል።[3] ስለዚህም በአጭሩ አንዱ ትውልድ የተቀበለውን እምነት ለሚመጣው ትውልድ ደግሞ ሲያሸጋግር ማለት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን በማቴዎስ 28፡19 ላይ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ **እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ**።" በማለት ጌታችን ሲናገር እንመለከተዋለን። ለሐዋርያት አሕዛብን ሁሉ እንዲያጠምቁ አገልግሎት ሲሰጣቸው እስኪሞቱ ድረስ አብሯቸው እንደሚሆን በመናገር ሳይሆን እስከ ዓለም ፍጻሜ አብሯቸው እንደሚሆን በመናገር ነው። ታድያ ግን ሃዋርያት እስከ ዓለም ፍጻሜ ቆይተው ይህንን አገልግሎት የማያደርጉ ከሆነ በምን መልኩ እስከ ዓለም ፍጻሜ ክርስቶስ አብሮ ይሰራል ወይም ይኖራል ካልን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሃዋርያት ሲያልፉ ሌሎች ደግሞ በሃዋርያት በራሳቸው የተሾሙ አባቶች ስላሉ በእነሱ በኩል ጌታ ሥራውን ይቀጥላል። እነሱም ሲያልፉ ደግሞ ከእነርሱ በኋላ በሚነሱት አባቶች እያለ ሃዋርያዊ ቅብብሎሹን ጠብቆ እስከ ዓለም ፍጻሜ ጌታ ክርስቶስ በዝች ሃዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ

[2] Strong's dictionary G3862

[3] Thayer's Greek Lexicon

ይሰራል። በምን መልኩ ይሰራል ካልን ስለሁላችን ሞቶ ከተነሳ በክብርም ካረገ በአባቱም ቀኝ ከተቀመጠ በኋላ በመንፈሱ በኩል ከእኛ ጋር አንድ ይሆናል። በመንፈሱ

በኩል ሁላችንን ክርስቲያኖችን ከእርሱ ጋር ያኖረናል(ሮሜ 8፡9)። ይሄ አንድነት ከትላንት ከሃዋርያት ጀምሮ እስከዛሬ ለወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ በዚህ መልኩ ሳይቋረጥ የሚቀጥል ሃይማኖት(እምነት)ነው። ከላይ በጠቀስነው ጥቅስ ላይ ጌታ "እያጠመቃችሁ" ብቻ ሳይሆን ያለው "ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ **እያስተማራችኋቸው**" ነውና "ትምሕርት" ደግሞ አለው። ይህም ትምሕርተ ሃይማኖት ነው። ይሁዳ በመልእክቱ ቁጥር 3 ላይ **"...ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት** እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ" በማለት ይናገራል። እዚህ ጋር ይሁዳ ስለዚህ ሃይማኖት ይጽፍ ዘንድ ግድ የሆነበትን ምክኒያት ሲጽፍ ከሃዋርያት ትምሕርት የተለየ የምንፍቅና ትምሕርትን የሚያስተምሩ ሰዎች ሾልከው ገብተው ነበርና ነው። ስለዚህም ስለ ኃይማኖታችሁ ተጋደሉ በማለት ያገራል። ወደ ታች ደግሞ "በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ" በማለት በኃይማኖታችን ራሳችንን ለማነጽ እንድንተጋ ያስረዳል።(ቁጥር 20) ይህንን ከሐዋርያት ጀምሮ እየተላለፈ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቀበልነውን እምነት ሐዋርያዊ ትውፊት እንለዋለን። ይህም ትውፊት በቃልም በጽሑፍም የተላለፈ ነው። ሐዋርያው እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡ "**በቃላችንም** ቢሆን ወይም **በመልእክታችን** የተማራችሁትን ወግ(ትውፊት) ያዙ። "(2ተሰ 2፡15)

ታድያ ግን በፕሮቴስታንቱ አለም ትውፊትን እንደማይቀበሉና "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የእምነት መሰረት እንደሆነ ይናገራሉ። በተደጋጋሚም ሲናገሩ የምንሰማው "መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፏል..?? ካልተጻፈ አልቀበልም" ሲሉ ነው። ይህ አስተሳሰብ እንዲዲህ የሚያስፈልገን ሁሉ በመጽሐፍ ውስጥ ተጽፎልናል ብሎ ለመናገር ይመስላል። ይህንን ሃሳብ ፍጹም ሃሰት እንደሆነ በማሳየት ከሥር በሚኖረን ትምሕርት በሚገባ እናፈራርሰዋለን። "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚለው ትምሕርት ፈጽሞ ከክርስትና የተለየ አስተሳሰብ ነው። ምክኒያቱም የጌታ ፍቃድ ገና ከጅምሩ **በመንፈሱ** በኩል ከእርሱ ጋር አንድ ሆነን እንድንኖር እንጂ በመጽሐፍ በኩል እንድንኖር አልነበረምና። ቤተ ክርስቲያን ያለ መጽሐፍ ቅዱስ የኖረችበት ጊዜ አለ፤ የሃዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ቤተ ክርስቲያን ተመስርታ ብዙ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ካመኑ በኋላ ነው በራሷ በቤተ ክርስቲያን የተጻፉት። በተለይም ድንቅ የሆነው የዮሐንስ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተች ሰባ አመታት በኋላ የተጻፈ ነው። ታድያ ግን

ምንም እንኳን ያለ መጽሐፍ ቅዱስ መኖር ብትችልም ያለ መንፈስ ቅዱስ ግን ኖራ አታውቅም ልትኖርም አትችልም ምክኒያቱም ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ሆኖ የሚኖረው በመንፈሱ በኩል ነውና። ለዛም ነው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ[4] እንዲህ በማለት የሚናገረው፡ “እግዚአብሔር ሕዝቡን ማግኘት የሚፈልገው በመጽሐፍ ሳይሆን ቀጥታ በራሱ ነው.. እነ ኖኅን እነ አብረሃምን እንዲሁም ልጆአቸውን እንዳገኛቸው.. በኋላም ራሱን ሙሴንም በራሱ እንዳናገረው.. ከዛ በኋላ ግን ሕዝቡ ከእነርሱ የማይጠበቅ ኃጢዓትን ሲያደርጉ ግንኙነቱ በጽሑፍ ደግሞ ሆነ። ይህ ነገር ለሃዋርያትም ጭምር ነው.. ጌታ ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራቸው ለሃዋርያቱ የሰጠው **መጽሐፍን ሳይሆን ቅዱስ መንፈሱን** ነው። በኋላ ግን ከዶግማ እና ከሕይወትም ጋር ተያይዞ ለማስታወሻነትም በጽሑፍ ሰፈረ።” በማለት ይናገራል። ከዚህም ደግሞ ክርስቶስ ለሐዋርያት የሰጠው መጽሐፍ ሳይሆን መንፈሱን እንደሆነ ልብ ልንለው ይገባል። መጽሐፉ የተጻፈው በፈሰሰላት መንፈስ በመነሳሳት በቤተ ክርስቲያን ነው። ስለ ትውፊት ምናልባትም ይህን ያህል ጠቅለል ያለ ሃሳብ ከሰጠን ሌሎች ማስረጃዎችን ከማስቀመጣችን በፊት በቅዱስ ትውፊት ሥር የሚካተቱት እነማን ናቸው የሚለውን ልናጠራ ይገባል። ያው ትውፊት ማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከጥንት ጀምሮ በቅብብሎሽ የመጣውን የቤተ ክርስቲያን ትምሕርትና ሥርዓትን እንደሚመለከት አይተናልና በዋናነት እነዚህን ሊያካትት ይችላል፡

- መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ(አዎ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ትውፊት ነው። ወደ ኋላ እንመለከተዋለን)
- የቤተ ክርስቲያን ጸሎቶች ወይም ቅዳሴያት(λειτουργία(ሌይቱርጊያ) – Liturgy)
- ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት ጋር የተስማሙ የቀደሙ አባቶች ጽሑፎች(writtings)፣ ስብከቶች(Homilies)፣ ትርጓሜዎች(commentaries, exegesis or expository works) እና የዕቅበተ እምነት ሥራዎች(Apologetic works)
- የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት ላይ የተላለፉ ትምሕርቶች። ሦስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያትን በትንሹ ለመጥቀስ ያህል፡

**ጉባኤ ኒቂያ**(325 ዓም)፡ አሪዮስ የተባለ መናፍቅ ወልድን ከአብ ለይቶ ፍጡር በመለኮቱ ብሎ ያስተማረ ሰው ነበር። የወልድን ውልደት ከመፈጠር ጋር በማገናኘት “ወልድ ሳይወለድ(ሳይፈጠር) በፊት ያልነበረበት ጊዜ ነበር በማለት ይናገር ነበር።

[4] Homilies on Mathew: Hom. 1 (በአጭሩ ነው ያስቀመጥኩት ሃሳቡን)

ታድያ ግን በኒቂያ የተሰበሰቡ ቅዱስ አትናቴዎስን ጨምሮ 318ቱ ቅዱሳን ሊቃውንት አባቶች ትምሕርቱን በመጽሐፍ ቅዱስና በሃዋርያዊ ትውፊት በመመዘን የቀለለና ታላቅ ኑፋቄ እንደሆነ በማመልከት አረሙን ከሰብሉ የለዩበት ጉባኤ ነው። በዚህም ጉባኤ ላይ ያረቀቁት የኃይማኖት ድንጋጌ(creed) አለ። ይህም እንደ አዲስ የረቀቀ ሳይሆን የነበረውን አጉልቶ ማሳየት ነበር።

**ጉባኤ ቁስጥንጥንያ**(381 ዓም)፡ በዚህ ጉባኤ “መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ነው” ብሎ ያስተማረ መቅዶንዮስ እና ወልድ ሥጋን እንጂ ነፍስን የራሱ አላደረገም የሚል አቡሊኖርዮስ በቁስጥንጥንያ በተሰበሰቡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ እንዲሁም ቅዱስ ጢሞትዮስ ዘአልቦ ጥሪትን ጨምሮ 150 ቅዱሳን አባቶች በተገኙበት ምንፍቅናቸው የተወገዘበት ነው።

**ጉባኤ ኤፌሶን**(431 ዓም)፡ በዚህ ጉባኤ ጌታችን ኢየሱስን ሁለት አካልና ሁለት ባህሪ ብሎ ያስተማረ፤ በዚህም ምክኒያት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ(Θεοτόκος- mother of God) አልልም ያለ ንስጥሮስ በኤፌሶን በተገኙ ቅዱስ ቄርሎስን ጨምሮ በሞቶ አባቶች የተወገዘበት ጉባኤ ነው።

**<u>ስለ ቅዱስ ትውፊት ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ፡</u>**

እንግዲህ ትውፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ብለን የተወሰኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን ከማስቀመጣችን በፊት ልንረዳ የሚገባን ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ትውፊት እንደሆነ ነው። ለምሳሌ ሃውርያው ጳውሎስ የዓይን ምስክር አይደለም፤ ከጌታም ሥር ተቀምጦ አልተማረም ግን በመንፈስ ቅዱስ በኩል ቀጥታ ከክርስቶስ ሃዋርያ በመሆን ትውፊትን እንደተቀበለ እናያለን። በ 1 ቆሮ 11፡23 ላይ “ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን(ማቀበል) እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና(መቀበል)” በማለት እንደተናገረ። ትውፊት እንደምናውቀው በቃል(oral) የሚመጣና በጽሑፍ(written) የሚመጣ ነው፤ ሃውርያው “**በቃልና በመልእክት** የተማራችሁትን **ትውፊት**” እንዲል(2 ተሰ 2፡15)። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ከጽሑፋዊ ትውፊት(written tradition) የሚመደብ ነው። አንዳንድ ሰዎች “መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ” በማለት ትውፊትን አንቀበልም ማለታቸውን ስንመለከት ያስገርመናል። የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ከተጻፉ በኋላ እንዲህ አሁን በያዝነው መልክ ተሰብስበው ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ተብሎ በቀኖና መልክ የተሰጠን ከሦስት መቶ አመታት በኋላ ነው። እስከዛ ድረስ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እንኳን canonized

ባይደረግም አባቶች ግን በትውፊት መልክ በመውረስ ይጠቀሙበት ነበር። የሚያስገርመን ግን መጽሐፍቱ ተሰብስበው በቀኖና መልክ ሲዘጋጁ አንድም ኦሪጅናል መጽሐፍ አለመገኘቱ ነው። ጠቅላላ የተገኙት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዳግም በአባቶች በቅጂ(copy) መልክ የተጻፉ ናቸው። ታድያ ግን ምንም እንኳን ኦሪጅናል ጽሑፎች ባይገኙም አባቶች እነዚህ መጽሐፍት ከአባቶች ወደ እኛ የተላለፉ ናቸውና መጽሐፍ ቅዱስ ይሄ ነው ብለው ወሰኑ። እንግዲህ ሐዲስ ኪዳን ሲጻፍም በቤተ ክርስቲያን በኩል ነበር አሁንም ውሳኔ ሲተላለፍም በቤተ ክርስቲያኗ በኩል ነው። ይህ ሁሉ የሚደረገው ግን ቤተ ክርስቲያን ከሙሽራዋ ከክርስቶስ በተቀበለችው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው። በዚህ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱስን ትውፊትነት ካየን እስቲ ደግሞ ከዚሁ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ቅዱስ ትውፊት ምን እንደተባለ ጥቅሶችን እንመልከት:

- 1 ቆሮ 11:2 - ወንድሞች ሆይ፥ በሁሉ ስለምታስቡኝና **አሳልፌ እንደ ሰጠኋችሁ ወግን(ትውፊትን) ፈጽማችሁ ስለ ያዛችሁ** አመሰግናችኋለሁ።

- 1 ቆሮ 11:34 **- ... የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ።**
  (ይህ የቀረ የተባለው የሐዋርያት ድንጋጌ ሲደረግ በጽሑፍ የሰፈረ አይደለም። እንደምንመለከተው "በመጣሁ ጊዜ" በማለት በአካል ተገኝቶ እንደሚያደርገው ይናገራል)

- 2 ተሰ 2:15 - እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ **በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ(ትውፊት) ያዙ።**

- 2 ተሰ 3:6 - ወንድሞች ሆይ፥ **ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ(ትውፊት)** ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ **ትለዩ ዘንድ** በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።

- 2 ጢሞ 2:2 - ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን **ከእኔም የሰማኸውን** ሌሎችን ደግሞ **ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።** (በአደራ መልክ ከአንዱ ወደ አንዱ እየተላለፈ ስለመምጣቱ)

- ይሁ 3 - ...ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ **ስለ ተሰጠ ሃይማኖት** እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። (ቅብብሎሽን ያሳያል)

- 2 ዮሐ 1፡12 - **እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ** በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወድም፥ ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተ ልመጣ **አፍ ለአፍም ልናገራችሁ** ተስፋ አደርጋለሁ። (ቅዱስ ዮሐንስ ይጽፍላቸው ዘንድ የሚወደው ብዙ ነገር እንዳለ ያስቀምጣል። ታድያ ግን ከመጻፍ ይልቅ አፍ ለአፍ(በቃል) ይነግራቸው ዘንድ ደግሞ ተስፋ እንደሚያደርግ ይነግረናል። ስለዚህ ሃዋርያት ትምሕርታቸውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያስተላለፉት በሁለቱም መንገድ እንደሆነ ያስረዳል)

- 3 ዮሐ 1፡13-14 - **ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ፥** ዳሩ ግን በቀለምና በብርዕ ልጽፍልህ አልወድም፤ ነገር ግን ወዲያው ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ፥ **አፍ ለአፍም እንነጋገራለን።**

## <u>ስለ ቅዱስ ትውፊት ማስረጃ ከሃዋርያት በኋላ ከተነሱ አባቶች</u>

**የኒቂያው እና ቁስጥንጥንያው የእምነት ድንጋጌ፡**[5]

በዚህ ላይ አባቶቻችን ያስቀመጥሉን "በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እናምናለን" የሚል ሳይሆን "አንዲት በምትሆን ሐዋርያዊትና ዓለም አቀፋዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን" የሚል ነው።

**ቅዱስ ሄራንዮስ**(130-202 ዓም):

"እውነታው ያለው በዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንጂ ሌላ በየትም አይደለም"[6] ይህ ምድቡ ከሐዋርያዊ አበው(Apostolic Fathers) የሆነ አባት በተዘዋዋሪ በቅዱስ ፖሊካርፕስ በኩል ከዮሐንስ ወንጌላዊ የተማረ ሰው ነው። የእውነት ሁሉ መገኛን ሲናገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ

[5] The holy Niceno-Constantinopolitan Creed
[6] Against heresies 3:4

ሳይሆን ያለው ቤተ ክርስቲያን ነው ያለው። ምክኒያቱም የእውነት ሁሉ መሰረት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናትና ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን ከተገኙ እውነታዎች ውስጥ **አንዱ** ነው። ሃዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ተመሳሳይ ነገር ሲናገር እንመለከተዋለን። እንዲህም አለ፡ “ብዘገይ ግን፥ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ **ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት፥** የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው።”[7]

በመቀጠልም ይህ አባት እንዲህ አለ፡

“እንበለውና በአስፈላጊ ጥያቄ ላይ በመካከላችን አለመስማማት ተፈጠረ። ታድያ ሃዋርያት አብዝተው ያዘወትሩባቸው ወደነበሩ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በመመለስ አሁን ላይ ስለ ተነሳው ጥያቄ ግልጽ ማብራሪያ እናገኝ ዘንድ ከእነርሱ መማር የለብንምን? ምናልባት ሃዋርያት ያስተላለፉልን ጽሑፎች ባይኖሩስ ኖሮ፤ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያስተላለፉትን ትውፊቶች እንከተል ዘንድ የግድ አይደለምን?”[8] ሄራንየስ እውነታው ያለው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ እንደሆነ ሲናገርና ትውፊትን መቀበል እንዳለብን ሲሞግት ይህንን አቀረበ። በመቀጠልም እንዲህ አለ፡

“በክርስቶስ ያመኑ ብዙ የበርባርያን ብሔሮች፤ በወረቀትና ቀለም ያልሆነ ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ በልባቸው ላይ ተጽፎ እንዲሁም የቀደመውን የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት በጥንቃቄ ጠብቀው ድህነትን ያገኙ እነርሱ ተስማሙ”[9]

ቅዱስ ሄራንዮስ እዚው አካባቢ አያይዞ ከተናገረው ውስጥ አንድ እንጨምር:

“ከቫለንቲኑስ(Valentinus)[10] በፊት የቫለንቲኑስ ተከታዮች የሉም፤ እንዲሁ

ከመርቅያኖስም(Marcion)[11] በፊት የመርቅያኖስ ተከታዮች የሉም።”[12]

በዚህ ገለጻው ላይ ደግሞ ድንቅ ነገር ያመለክተናል። ያው ከቫለንቲኑስ በፊት የቫለንቲኑስ ተከታዮች የሉም ማለቱ መስራቹ ወይም አስጀማሪው ራሱ ቫለንቲኑስ ነው ማለት ነው። ስለዛ ወደ ኋላ እስከ

---

[7] 1ጢሞ 3፡15

[8] Against heresies 3:4:1

[9] Against heresies 3:4:2

[10] ቫለንቲኑስ ድኅነት በእውቀት ዓይነት ትምሕርት የነበረው ኖስቲክ ነው። ሄራንዮስም በስፋት ለዚህ ሰው መልስ ሰጥቷል

[11] መርቅያኖስ ደግሞ የብሉይ ኪዳንን አምላክ ክርስቶስን ከላከው ጋር በመለያየት ክርስቶስን የላከው አምላክ በብሉይ ከነበረው አምላክ ይበልጣል በማለት ያስተምር ነበር።

[12] Against heresies 3:4:3

ሃዋርያት ድረስ ሊቆጥሩ አይችሉምና ሃዋርያዊ ሳይሆን የሚባሉት ቫለንቲኑሳውያን(Valentinians) ነው የሚባሉት። ይሄንን ነገር በመያዝ እኛም ደግሞ እንዲህ ልንል እንችላለን "ከሉተር በፊት የሉተር ተከታዮች የሉም" ስለዛ አሁንም ፕሮቴስታንቱ ሃዋርያዊ ሳይሆን የሚባለው ሉተራዊ፣ ካልቪናዊ እና ሌሎችም የፕሮቴስታንት ቤተ እምነት ቡድኖች መስራቾችን እየያዝን በእነሱ ልንጠራቸው እንችላለን ነው። ስለዛ ሃዋርያዊ የሚያስብለው መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ መያዝ ሳይሆን ሃዋርያዊ ትውፊትንም መያዝ ነው።

**ቅዱስ አትናቴዎስ፡**

"ሁላችን በክርስቶስ ክርስቲያኖች ስንባል፤ መርቅያኖስ የምንፍቅና ትምሕርትን አነሳ ተወገዘም፤ መርቅያኖስን ያወገዘውን የተከተለ ክርስቲያን እንደሆነ ሲቀጥል ከመርቅያኖስ ጋር አብሮ የወጡት ግን ክርስቲያን መባላቸው ቀርቷል ይልቁንም መርቅያኖሳዊ(Marcionites) ይባላሉ እንጂ። ልክ እንዲሁ ሌሎች መናፍቃንም ስማቸውን ለተከታዮቻቸው ሰጥተዋል። እንዲሁ እስክንድሮስ(Alexander) አርዮስን ሲያወግዝ ከእስክንድሮስ ጋር የቀሩት በክርስቲያንነታቸው ሲቀጥሉ ከአርዮስ ጋር የተለዩት ግን የጌታችንን ስም ለእኛ በመተው እነሱ አርዮሳውያን(Arians) ይባላሉ"[13] (እንዳይበዛ ምንም የሃሳብ ለውጥ ሳላደርግ አሳጥሬዋለው) ሃሳቡ ደግሞ ከላይ ከጠቀስነው ከሄራንዮስ ጋር ተመሳሳይነት አለው። መጽሐፍ ቅዱሱን መቀበል ብቻ ክርስቲያን አያስብልም። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱሱን በቤተ ክርስቲያኗ በኩል(በእሷ ትርጓሜ) ሲቀበል ነው ክርስቲያን የሚያስብለው።

**ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፡**

"..በቅብብሎሽ(succession) ውስጥ ከአባቶች የተቀበልነውን ትውፊት ለሁል ጊዜ አጥብቀን መያዝ አለብን.."[14]

**ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ፡** "በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጠብቆ የመጣውን እምነት(δόγμα – dogma)

[13] Four discourse Against Arians: Discourse 1:chap. 1: 3
[14] On "Not Three Gods." To Ablabius: par. 3

አንዳንዱን በጽሑፍ ተቀበልን ሌላውን ደግሞ በሃዋርያት ትውፊት ወደ እኛ የደረሰውን ተቀበልን። ከእውነተኛው ሃይማኖት አንጻር ሁለቱም ተመሳሳይ ሃይል አላቸው"[15]

"በመስቀል ምልክትስ እንድናማትብ ማን በጽሑፍ አስተማረን...... ይልቁንም በቃል ከተላለፈው ደግሞ ወሰድን"[16]

**ቅዱስ ኤጲፋኒዮስ፡** "ሁሉም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝምና ትውፊትን የግድ ልንጠቀም ይገባል። ቅዱሳን ሃዋርያትም የተወሰኑትን በጽሑፍ ሌሎችን ደግሞ በትውፊት አቀብለውናልና።"[17]

**ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡** "ጳውሎስ እንዲህ በማለት አዘዘ 'እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ትውፊት ያዙ'[18] ከዚህም ሁሉን ነገር በመልእክታቸው እንዳላስተላለፉና ይልቁንም ብዙ ያልተጻፉ እንዳሉ ግልጽ ነው። በጽሑፍ እንዳሉት ሁሉ ያልተጻፉትም ደግሞ እምነት የሚጣልባቸው ናቸው።"[19]

**ቅዱስ ጄሮም፡** "ከዓለም ጫፍ ከኢትዮጵያ ድረስ የንግስቷን ቦታ ጥሎ ወደ ቤተ መቅደስ የመጣው፤ በሰረገላ ውስጥ ሆኖ እንኳን ሳይቀር መጽሐፍ ቅዱስን ያነብ የነበረ የመለኮታዊ እውቀት ታላቅ አፍቃሪ የሆነው ቅድሱ ጃንደራባ(ቅዱስ ባኮስ) ከኢሳያስ ትንቢት ያነብ ነበር ታድያ ግን ስለ ማን እንደሚያወራ እንኳን አያውቅም ነበር። ሳያውቀው በመጽሐፍ ውስጥ አመለከው.. ፊሊጶስም አገኘው የሚያነበውንም ገለጠለት.. መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን ሊያሳድገን አይቻልም የሚመራን ከሌለ በስተቀር(እንደ ቅዱስ ባኮስ)"[20]

---

[15] On the Holy spirit: Chap. 27፡66
[16] Ibid
[17] Panarion: 61:6(5)
[18] 2 ተሰ 2፡15
[19] Homilies on 2 Thessalonians 2:15, hom. 4
[20] Letter 53 To Paulinus: 5-6

**አውግስጢኖስ**: "የዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን ድምጽ ባያሳምነኝ ኖሮ በወንጌልም ባላመንኩ ነበር"[21]

## ማጠቃለያ: አሥር የ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" ውድቀቶች፡

በዚህ ማጠቃለያ ውስጥ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚለው የፕሮቴስታንቶች ትምሕርት ከላይ ከተመለከትነው አንጻር ምን ያህል ከሥጋና ደም ብቻ የመጣ ሰዋዊ አስተሳሰብ እንደ ሆነ በአጭሩ እንገልጻለን፡

- መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን ስለራሱ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን መልስ የለውም ለምሳሌ 4 ወንጌላት እንዳሉ ፕሮቴስታንቱ ያምናል። ወንጌላት 4 ብቻ ስለመሆናቸው ግን አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የለም። ወይም ደግሞ 27 የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት እንዳሉ ያምናሉ፤ ግን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የቱም ቦታ ላይ 27 የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት አሉ ብሎ አልተናገረም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚለው ሰዋዊ ትምሕርት ውድቅ ሆነ።

- ፕሮቴስታንቶች መጽሐፍቱን ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንደተቀበሉ ያምናሉ። ታድያ ግን በእነርሱ ሃሳብ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ስህተት ሊሆን ይችላል የሚል ነው። ታድያ ስህተት የማይሆነውን(inffalible) መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት ሊሆን በሚችል(Fallible) ትውፊት እንዴት መወሰን ይቻላል? ምናልባት እንደ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን የእውነት ሁሉ መገኛ ናት ብለው ካላመኑ በስተቀር።

- "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚል ትምሕርት ፈጽሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም በመጽሐፍ ቅዱስ አንድም ቦታ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚል የለም። ይህ ማለት "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚለውን ትምሕርት በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አያብራሩትም። "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" ብለው እየተናገሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን አንድም ድጋፍ

[21] Contra Epist. Manichae quam V Cant Fundamentals (Fr Tadros Malaty – Tradition and orthodoxy)

የሌለው መሆኑን ስንመለከት ይህ ትምሕርት ሰዋዊ ብቻ ሳይሆን ሰነፍ_ሰዋዊ የሚያስብለውም እንደሆነ እንመለከታለን።

- ሦስተኛ ላይ ካነሳነው ጋር ተያይዞ፡ ታድያ ምነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሌለ ሃሳብ ከሆነ ፕሮቴስታንቶች ሁሉ ለምን ተቀበሉት? የሚለውን ሃሳብ ስናነሳ ይህ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምሕርታቸው ለእነርሱ ሳያስቡት ትውፊት ሆኗል። የሚነሳው ሁሉ በሥላሴ የሚያምነውም የማያምነውም ፕሮቴስታንት "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ከእርሱ ከሚቀድሙት ፕሮቴስታንት አባቶቹ በትውፊት ከተቀበለው ነውና ይህ ደግሞ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ትውፊትን በመቀበላቸው ከራሳቸው "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" ከሚለው ትምሕርታቸውም ጋር በሚገባ የሚጋጭ ነው።

- "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚለው ትምሕርት ታሪካዊም አይደለም። ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የትውፊትን አስፈላጊነት አስቀምጠው አልፈዋል። ይህ ትምሕርት ግን የፕሮቴስታንቲዝም አባት ተብሎ በሚታወቀው በሉተር የተጀመረ ነው። ጅማሬውም የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ከተጻፉ 1500 ዓመታት በኋላ በ16ኛው ክ/ዘመን ነው። ስለዚህም ይህ አባባል ሐዋርያትን ራሳቸውን ጨምሮ እስከ ሉተር ድረስ 1500 አመት ሙሉ የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ስህተት ውስጥ ወድቀው ነበር የሚያስብል ነው። ይህ ነገር ደግሞ ትክክል ከሆነ፤ እኛ ከሉተር ጋር ሆነን ትክክል ከምንሆን ከሐዋርያት ጋር ሆነን ስህተት መሆንን እንመርጣለን።

- ጴጥሮስ እንዲህ አለ፡ "በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም።" ታድያ ለገዛ ለራሱ ማንም አይተርጉም ከተባለ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በራሱ ትርጓሜ አይደለምና ትርጓሜን ጥለው "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚሉ ሰዎች በዚህም ይረታሉ።

- ፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ ቅዱስን ማንም ሰው በራሱ መተርጎም እንደሚችል ያስተምራሉ። ይህም ደግሞ የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እንደሆነም ይገልጻሉ። ለዚህ ንግግራቸው ምናልባት ጥያቄ እናንሳ ብንል፡ (??) ታድያ ምነው ፕሮቴስታንት የዚህን ያህል ተከፋፈለ?

ለምንስ አንድ መሆን አቃተው? አንዱ የሚተረጉምበትስ መንገድ ከሌላኛው ለምን ተለያየ? ሁሉም ግን የሚሉት መንፈስ ቅዱስ እንደሚያስተምራቸው ነው። ታድያ አንዱ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይከፋፍላልን? ወይስ በእርግጥም ትርጓሜው ከአንዱ መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ከብዙዎች አጋንንታዊ መናፍስት? ምክኒያቱም ጳውሎስ አስቀድሞ የተናገረው ነገር ነበር፡ "መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች **የሚያስቱ መናፍስትንና** በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን **የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ** ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው"[22]

- በፕሮቴስታንቱ ዘንድ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ብለው የጻፏቸው መጽሐፍት አሉ። ታድያ ግን "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" ካሉ "የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ" እያሉ ሌሎች ተጨማሪ መጽሐፍትን ማዘጋጀቱን ምን አመጣው? ይህም በዚህ በወጣው ማብራሪያ የሚመሩ ሁሉ ደግሞ የእርሱን ትውፊት የሚከተሉ እንጂ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" ማለታቸውን ትተዋል ያስብላል።

- "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሱን ራሱ ከየት አመጡት..?? ከላይ እንዳየነው የሃዲስ ኪዳን መጽሐፍት ቀኖና እንኳን የተሰራላቸው በ4ኛው ክ/ዘመን ላይ ነው። ከዛ በፊት ግን በተለያዩ መጻሕፍት ላይ አጨቃጫቂ ነገሮች ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን ግን በኋላ ላይ ይሄ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ብላ ሰጠች። ይሄ በቤተ ክርስቲያን በኩል የመጣው ትውፊት ፕሮቴስታንቶችም ጋር ደርሶ እነሱም የዚህ ትውፊት ተጠቃሚ ሆነዋል። ታድያ ትውፊት ይዞ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" ማለት ምን ማለት ነው?

- በአጠቃላይ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚለው ትምህርት በአሁን ሰዓት ከ40,000 በላይ ለሚሆኑ ለተከፋፈሉ የፕሮቴስታንት ቡድኖች መመስረት ዋናው ምክኒያት ነው።

[22] 1ጢሞ 4፡1-2

## **መጽሐፍ ቅዱስ**

በዓለማችን ላይ ምናልባት ብዙ መጽሐፍትን እናውቅ ይሆናል። የልቦለድ፣ የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የጥንቁልና እና ሌሎችም። ታድያ ግን ከእነዚህ እና ከመሰሎቻቸው መጽሐፍት ሁሉ ተለይቶ **ቅዱስ** ተብሎ የሚጠራ መጽሐፍ አለ እርሱም እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆነው ቅዱሱ መጽሐፋችን ነው። ቅዱስ የተባለውም ምንም እንኳን ቅዱሳን ሰዎች ቢጽፉትም በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ነውና ባለቤቱ ራሱ ቅዱሱ አምላካችን እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። መዝሙረኛው ዳዊት "አንደበቴ እንደ ፈጣን ጸሐፊ ብርዕ ነው" እንዲል(መዝሙር 44(45):1) አንደበቱ ብርዕ ከሆነ ጸሐፊው አምላክ ነውና ነው.. እግዚአብሔር ቃሉን በአንደበቱ ያስቀምጣል በእርሱም በኩል ይናገራል ማለት ነው። ለዛም ነው በ2ሳሙ 23፡1-2 እንዲህ የሚለው፡ " የእሴይ ልጅ የዳዊት ንግግር፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ፤ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበረ።" ጴጥሮስም በተመሳሳይ እንዲህ ይለናል፡ "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።" (2ጴጥ 1፡21) ሃዋርያው ጳውሎስ ደግሞ በ 2ጢሞ 3፡16 "የእግዚአብሔር መንፈስ( θεόπνευστος) ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" በማለት እስትንፋሰ እግዚአብሔር እንደሆነ ያስረዳል።

ሁላችን እንደምናውቀው ይህ ታላቁ የእግዚአብሔር ቃል ቅዱሱ መጽሐፍ ሁለት ታላላቅ ክፍሎች ሲኖሩት እነሱም ብሉይ ኪዳን እና ሃዲስ ኪዳን ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ከመምጣቱ በፊት የተጻፉት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ሲባሉ ከጌታ ከድንግል መወለድ በኋላ ደግሞ በጌታ ደቀመዛሙርት የተጻፉት እነርሱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተብለው ይታወቃሉ። መጽሐፍ ቅዱሱ አንድ ወጥ መጽሐፍ ሳይሆን በውስጡ ያሉ መጽሐፍቶች እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው የተጻፉ መጽሐፍት ናቸው። እነዚህም በቀደመው ዘመን በጥቅል በጥቅል ሆነው ይጻፉና ይቀመጡ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በአንድነት ተጠርዞ ለሕትመት የበቃው የሕትመት ቴክኖሎጂው ከመጣ በኋላ ሲሆን ይህም በ15ኛው ክ/ዘመን አጋማሽ የተጀመረ ነው። በውስጡ የተለያዩ መጽሐፍት አሉ ካልን ደግሞ የተለያዩ ጸሐፍያንም አሉ እያልን እንደሆነ ግልጽ ነው። ለምሳሌ "የማቴዎስ ወንጌል" አንድ መጽሐፍ ሲሆን ጸሐፊውም ማቴዎስ ነው። የሉቃስ ወንጌልም ስንል እንዲሁ። በአጠቃላይ ከ40 በላይ በሚሆኑ ቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ነው። የቀረውን ደግሞ ብሉይ ኪዳን እና ሃዲስ ኪዳን ብለን ከፋፍለን እንመልከት።

## ብሉይ ኪዳን

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ሁሉም ማለት በሚቻልበት ሁኔታ የተጻፉት በእብራይስጥ ቋንቋ ነው። ከጊዜያት በኋላ ከበኩረ ቋንቋው ከዕብራይስጡ ወደተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። አሁንም ድረስ ካሉ ጥንታውያን ከሚባሉ አበይት ትርጓሜያትም የግሪኩ ሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ(ሴፕቱኤጀንት)፣ የግዕዙ[23]፣ አረማይክ(ታርጉም)፣ ሲሪያክ(ፔሺታ) እና የላቲኑ(ቩልጌት) ይጠቀሳሉ። ብሉይ ኪዳን ላይ ከምናስተውላቸው ጉዳይ ውስጥ አንዱ የብዛት ጉዳይ ነው። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት 46 ሲሆኑ የፕሮቴስታንቱ ዓለም ደግሞ 39 መጽሐፍትን በመቀበል የቀሩትን እነሱ የማይቀበሏቸውን ቅዱሳት መጽሐፍት ደግሞ የማይታወቁ ድብቆች(Apocryphal) ይሏቸዋል። በእኛ ሃገር ደግሞ "ኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጨምራ ነው" የሚሉ ምስኪኖችም አይጠፉም። ታድያ ግን ይህ ልዩነት እንዴት ተፈጠረ የሚለውን ከሥር መሰረቱ በመመልከት ማን ጨማሪ ማን ቀናሽ እንደሆነ ለማየት እንሞክራለን። ይህንን ለማየት እንዲረዳን አስቀድመን የሰብዓ ሊቃናትን ትርጓሜ እንመለከትና በኋላ ዘመን ላይ ስለተፈጠሩ ውዝግቦች እናያለን።

## ሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ(Septuagint, LXX.)

የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጓሜ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ300 ዓመት ገደማ ከቀደምቱ እብራይስጥ ወደ ግሪክ እንደተተረጎመ ይነገራል። የትርጉም ሥራውም የጀመረበት ምክኒያት በእስክንድርያ ዳግማዊ በጥሊሞስ የተባለ ንጉስ ታላቅ ቤተ መጽሐፍትን በማስገንባቱ የአይሁድን መጽሐፍትም በዛው ለማካተት ሲባል እንደነበረና በትርጉም ሥራው ላይም ከ12ቱም ነገደ እስራኤል ሰድስት ስድስት ተውጣተው ሰባ ሁለት የአይሁድ ሊቃውንት እንደተሳተፉና ተዓምራዊ የትርጉም ሥራ እንደነበረ ታሪክ ይናገራል። ይህም ለምሳሌ የአርስቲያስ ደብዳቤ(The Letter Of Aristeas) ተብሎ በሚታወቀው ጥንታዊ ጽሑፍ ላይ ተገልጿል። ሰባ ሁለት ሊቃውንት ተሰባስበው ትርጉሙን ቢጀምሩም አንዳንዶች አምስቱን የሕግ መጽሐፍትን ብቻ እንደተረጎሙና ሌሎቹን ደግሞ የግሪክ መጽሐፍት ሌሎች እንደተረጎሟቸው ሲናገሩ አብዛኞቹ ደግሞ አብዛኛውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ራሳቸው 72ቱ ሊቃውንት እንደተረጎሙት ይስማማሉ። ያም ሆነ ይህ ግን በጠቅላላው የግሪኩ ትርጓሜ መጽሐፍ[24] ሰብዓ ሊቃናት(septuagint)

---

[23] በታሪክ ደረጃ ግዕዙ ቀጥታ ከዕብራይስጡ ተተርጉሟል የሚሉ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ ከሰብዓው ሊቃናት እንደተተረጎመ ይናገራሉ

[24] ሰብዓ ሊቃናት ስንል በፕሮቴስታንቱ ዓለም ተቀባይነት የሌላቸው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትንም የሚያካትት ነው።

ተብሎ ይጠራል። ስሙም የመጣው ከላቲኑ ሰባ ቁጥር(Septuaginta, LXX.) ሲሆን ይህም ሰባ ሁለቱን ሊቃውንተ አይሁድ የሚያመለክት ነው።

የግሪክ ቋንቋ እጅጉን በተስፋፋበትና ኃያል በሆነበት በዛ ዘመን ይህ የግሪኩ ትርጓሜ እጅጉን ተቀባይነት የነበረውና አይሁዳውያን በምኩራቦቻቸው ሳይቀር ይጠቀሙበት የነበረ ነው። በሐዲስ ኪዳንም ዘመን ትልቅ ተቀባይነት የነበረው ይኸው ትርጓሜ ነው። አልፍረድ ኤደርሼይም( Edersheim, Alfred) የተባላ ፕሮቴስታንት ጸሐፊ እውቅ በሆነው መጽሐፉ(The Life and Times of Jesus the Messiah) ላይ የግሪኩን የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ መጽሐፍ እንዲህ ሲናገርለት እንመለከታለን፡ “የተከበረ የሚያደርገው ጥንታዊነቱ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ በመጣ ሰዓትም የእኛን ተቀባዩንም መጽሐፍ(Authorized version)[25] ቦታ የያዘ ስለነበረም ነው። እንዲሁ በነጻነትም በሐዲስ ኪዳን ተጠቅሷል። ይልቁንም የሕዝቡ መጽሐፍ ነበር ስንል በግሪክ(አይሁዶች) ዘንድ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም በገሊላ እንዲሁም በይሁዳም ጭምር ነው እንጂ”[26]

ምንም እንኳን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ግን ኦሪጅናል ከታቡ ጠፍቶ ድጋሜ ኮፒ[27] የተደረጉ የኮፒ ኮፒ ኮፒዎች ቀሩ። ስለዚህም በዛ ሰዓት ስለነበረው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ስናስብ ኦሪጅናል ብለን ልናስብ አይገባም። በጎን ደግሞ ይህ የግሪኩ ትርጓሜ ጥንታዊ ከመሆኑና በራሳቸው በአይሁዳውያንም የተመሰከረለት ከመሆኑ አንጻር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። ለዛም ነው ከላይ እንዳየነው በሐዲስ ኪዳንም በክርስቶስና በሐዋርያቱ ዘንድ ጥቅም ላይ ውሎ የምናገኘው። እስከዛሬም ድረስ እኛ ክርስቲያኖች ይህንኑ መጽሐፍ እንቀበለዋለን። ታድያ ግን ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተች በኋላ ብዙ ክርስቲያኖች ሐዋርያትንም ጨምሮ የግሪኩን ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እየጠቀሱ ስለ ኢየሱስ መሲሕነት ማስረዳት ጀመሩ ብዙ አይሁዳውያንንም ወደ ክርስትና መለሱ። በዚህ ጊዜ ነበር አይሁድ አስቀድማ ክርስቶስን እንደገደለች በኋላም ሐዋርያቱን እንዳሳደደች እንደገደለችም፤ ጸረ ክርስቶስ ሆና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚመልሱትን የሐዋርያት የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስን መቃወም ጀመረች። በሰዓቱ የዕብራይስጥ ቋንቋ በብዙ አይሁዳውያን ዘንድ በተዳከመበት በዛ ወቅት ሆን ብለው

[25] እዚህ ላይ “authorized version” በማለት የራሱን የተናገረው በፕሮቴስታንቱ አለም ለእነሱ authorized መጽሐፍ የሰብዓ ሊቃናቱ መጽሐፍ አይደለምና ነው። ምንም እንኳን ለእነሱ ባይሆንም በክርስቶስና በሐዋርያት ሰዓት ግን authorized መጽሐፍ የግሪኩ ነበር።

[26] Edersheim, Alfred: The Life and Times of Jesus the Messiah: page 49

[27] ኮፒ ስንል ልክ እንደ አሁኑ በማሽን ሳይሆን በእጅ ድጋሜ በመጻፍ ነው።

ክርስቲያኖችን ለመቃወም የግሪክ ሰብዓ ሊቃናቱን የራሳቸውን ትርጓሜ ማገድ ጀመሩ። ይህንንም በ2ኛው ክ/ዘመን የነበረው ሰማዕቱ ዮስቲን(Justin Martyr) በሰዓቱ ከነበረ አንድ የአይሁድ ሊቅ ጋር ባደረገው ውይይት(dialogue) ላይ አስፍሮታል።[28] በጣም የሚያስገርመን ግን የሰብዓ ሊቃናቱን ግሪክ አውግዘው ድጋሜ ለራሳቸው ደግሞ በሰዓቱ ካገኙት የኮፒ ኮፒ ዕብራይስጥ መጽሐፍ የግሪክ ትርጓሜ ማዘጋጀታቸው ነው። ከእነዚህም ውስጥ የአኪላ(Aquila)፣ የቴዎዶትዮስ(Theodotion)[29] እና የሲማከስ(Symmachus) ትርጓሜዎች ይገኙበታል። እነዚህም በአርጌንስ Hexapla በተሰኘው የብሉይ መጽሐፍ ስብስብ ሥራ ውስጥ ከሰብዓ ሊቃናት ጋር የተካተቱ ናቸው። አሁን ላይ የተወሰኑ ብጥስጣሾች(Fragments) ብቻ ነው ያሉት። አሁን ባለንበት ጊዜ ሆነን ስንመለከተው እነዚህ የግሪክ ትርጓሜያትም ሆኑ በዛ ሰዓት የነበረው እብራይስጥ መጽሐፍ ጥንታዊ ከመሆናቸው አንጻር ተቀባይነት ይኖራቸው ይሆናል ግን ደግሞ ሆን ብለው ያሳሳቱትንም ሆነ በኮፒስቶች ስህተት የገቡ ስህተቶቻቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በመክተት ነው። በሰዓቱ ከነበሩ ስህተቶች ውስጥ አንዱ በትንቢተ ኢሳያስ 7፡14 ላይ የተጠቀሰው ሲሆን ይህም "ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች" በማለት መሲሕ ኢየሱስ ቀጥታ ውልደቱ ከድንግል እንደሆነ ከውልደቱ 700 ዓመት ቀደም ብሎ መተንበዩን ሲያመለክት ይህ ቃል ግን በዚህ መልኩ የሚገኘው የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጓሜ ላይ ሲሆን ግሪኩ ታድያ ግን ክርስቶስ በተወለደበት ጊዜና ከዛ በኋላም የተገኙ የእብራይስጥ ኮፒ ክታባት "ድንግል" የሚለውን ቃል "ወጣት ሴት" ብሎት ተገኘ። ክርስቲያኖች የክርስቶስን በድንግልና መወለድ ከብሉይ ኪዳን ራሳቸው አይሁዳውያንም ከያዙት የግሪክ መጽሐፍ እየጠቀሱ ሲያስረዱ አይሁዳውያን ግን የሰብዓ ሊቃናትን አንቀበልም የእብራይስጡም ድንግል ሳይሆን "ወጣት ሴት" ነው የሚለው በማለት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ማመጽን ተያያዙት። ይህም ደግሞ ከላይ በጠቀስነው ሰማዕቱ ዮስቲን ከታርፎን(ትሪፎን, Trypho) ጋር ባደረገው ውይይት ላይ የክርስቶስን በድንግልና መወለድ ዮስቲን ሲያስረዳው ትሪፎን የተባለው አይሁድ ግን ኢሳያስ 7፡14 "ድንግል" ሳይሆን "ወጣት ሴት" እንደሚል ሲሞግት እናየዋለን።[30] ይህም ብቻ ሳይሆን ክርስትና ከተጀመረ በኋላ ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጎሙት ከላይ ያየናቸው የእነ አቂላ እና ቴዎዶትዮን የግሪክ ትርጓሜዎችም ላይ "ወጣት ሴት" ብለው የተረጎሙት ሲሆን ይህንን ተከትለው ኢብዮናይት የተባሉ ቀደምት መናፍቃንም ክርስቶስ ከዮሴፍ ተወለደ ብለው ያምኑ እንደነበረ

---

[28] Justin Martyr: dialogue with Trypho: chap. 71

[29] ይህ የግሪክ ትርጓሜ ቀጥታ ከእብራይስጥ ሳይሆን ራሱን ሰብዓ ሊቃናትን እንደ አዲስ አስተካክሎ ያዘጋጀው ነው የሚሉ አሉ

[30] Ibid chap. 66 & 67

ጥንታዊው አባት ሄራንዮስ ይናገራል።[31] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ከማርያም ድንግልና ጋር ተያይዞ ኢሳ 7፡14 ላይ ስላለው ቃል  አንዳንደ ሰዎች ሌሎች ትርጓሜዎችን በማምጣት "ድንግል ሳይሆን ወጣት ሴት ነው የሚለው" የሚሉ እንደነበሩና ተዓማኒነት ያለው ግን ከክርስቶስ መምጣት በኋላ በጠላትነት ያደረጉት ትርጓሜ ሳይሆን ክርስቶስ ከመምጣቱ ብዙ ዓመታት በፊት የተረጎሙት የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጓሜ ነው እያለ ያስረዳል[32]

ሰብዓ  ሊቃናቱ ላይ ድንግል ተብሎ የተተረጎመው ቃል παρθένος(ፓርቴኖስ) የሚል ቃል ሲሆን አይሁዳውያኑ ግን ቃሉ መሆን የነበረበት νεᾶνις(ኔአኒስ) ነው ይላሉ። ይህም ከእብራይስጡ "አልማህ" ከሚለው ቃል ጋር እንዲስማማ ነው። በእርግጥ በእብራይስጥ "አልማህ" ተብለው የተጻፉ ብዙ ቦታዎች ላይ ግሪኩ "ኔአኒስ"(ወጣት ሴት) ብሎ ነው የተረጎመው። ታድያ እዚህ ክፍል ላይ ስለምን "ፓርቴኖስ"(ድንግል) ተብሎ ተተረጎመ የሚል አይጠፋም። ለዚህ የእኔን እይታ ለማስቀመጥ ያህል፡ አይሁዳውያን ገና ከጅምሩ ሲከራከሩ የነበሩት የኮፒ ኮፒ የሆነ እብራይስጥ መጽሐፍን ይዘው እንጂ ኦሪጅናሉን አግኝተውም አይደለም። እሱ ቀርቶ ያን ያህል ጥንታውያን ኮፒዎችንም ለመያዛቸው ማስረጃ የለም። እነሱ ከያዙት ኮፒ በእድሜ የሰብዓ ሊቃናቱ እንደሚቀድም ግልጽ ነው። ምክኒያቱም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ 300 ዓመት በፊት የተተረጎመና በአይሁዳውያንም ዘንድ ትክክለኛ እንደሆነ የተረጋገጠለት በራሳቸውም በአይሁዳውያን የተተረጎመ በመሆኑ። ስለዚህም ገና ከጅምሩ ኢሳያስ ትንቢቱን ሲናገር "ወጣት ሴት"(አልማህ) ብሎ ሳይሆን "ቤቱላህ"(ድንግል) በማለት ነው። ታድያ ግን በሰው ሰወኛው ለሚያስብ ሰው ድንግል ልትወልድ እንደማትችል ግልጽ ነውና አይሁዳውያን ከዚህ አንጻር ከጊዜ በኋላ ድንግል የሚለውን "ወጣት ሴት" ብለውታል የሚል እይታ አለኝ። ቃሉ ግን ቀጥታ "ድንግል" እንደሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አለን። ይህም በሐዲስ ኪዳን በማቴዎስ ወንጌል ላይ መልአኩ ዮሴፍን ሲያጽናና እና ድንግል ማርያም ከወንድ እንዳልጸነሰች ሲያስረዳው ከትንቢተ ኢሳያስ በመጥቀስ "በነቢይ 'እነሆ ድንግል(παρθένος) ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል' የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆኗል" በማለት ነበር።(ማቴ 1፡23) ስለዛ ይህ ቃል በሃዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ሲነገረን ማቴዎስ ራሱ የሰብዓ ሊቃናትን ትርጓሜ እንደሆነ የሚቀበለው እና

---

[31] Against Heresies 3: 21:1

[32] St. John Chrysostom: hom. On Matthew: 5:4

እርሱ ብቻ ሳይሆን መልአኩም ሳይቀር የጠቀሰው በሰዓቱ ካለው እብራይስጥ ሳይሆን ከግሪኩ እንደሆነ ስንመለከት ችግር ያለው እብራይስጡ ጋር እንደሆነ እንረዳለን።

ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ ስለ ሰብዓ ሊቃናቱ ትርጓሜ ሲናገር በእግዚአብሔር እቅድ ለግሪክ ሰሚዎች የሕግም የትንቢትም መጽሐፍት በሰባው ሊቃውንት እንደተተረጎመ ይናገራል።[33]

ቅዱስ ሄራንዮስ ሃዋርያዊ አባት እንዲህ ይላል "በነቢያቱ አድሮ ትንቢት ያናገረ በሰብዓ ሊቃናትም በትክክል ትንቢቱን ያስተረጎመ በሃዋርያትም የመንግስትን ወንጌል ያሳወጀ አንድና ተመሳሳይ መንፈስ ነው።"[34]

በማለት ትርጓሜው ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ተነሳሽነት እንደተተረጎመ ይናገራል። ይህ አባት የግሪክ ሰብዓ ሊቃናቱን ትርጓሜ አይሁዳውያን አንቀበልም ማለታቸውን አጥብቆ ይቃወምና ክርስቲያኖች ይህንን እየጠቀሱ ሲረቷቸው ይህንን ሃሳብ እንዳመጡም ይናገራቸዋል። ስለ ሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ ከተናገረው ነገር ውስጥ አንድ ልጋብዛችሁ፡

"መጽሐፍቱ(የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጓሜ) እንዲህ ባለ ታማኝነትና በእግዚአብሔር ጸጋ ተተርጉመዋልና፤ ከእነዚህም መጽሐፍት ደግሞ እግዚአብሔር ለልጁ አዘጋጅቶናል፤ ብሎም እምነታችንን ሰርቷልናል፤ **እንዲሁ ያልተበረዘን መጽሐፍ በግብጽ[35] ጠብቆልናል**። ግብጽ፡ በከነዓን ከነበረው ረሃብ በሸሸ ጊዜ የያዕቆብ ቤት የታነጸበት፤ ጌታችንም ሄርዶስ ባሳደደው ጊዜ ሸሽቶ የተረፈበት.. (አሁን ደግሞ መጽሐፉን ጠበቀበት ነው)"[36]

በማለት በሰዓቱ ከነበረው የእብራይስጥ መጽሐፍ የግሪኩን ካስበለጠ በኋላ ዝቅ ሲል ደግሞ እንዲህ ይላል፡

---

[33] The Stromata: bk. 1: chap. 22

[34] Ibid no. 4 (ሃሳቡን ቀጥታ በማስቀመጥ ጽሑፉን በትንሹ አሳጥሬዋለው) ከዚህም የምንረዳው ሰብዓ ሊቃናት የተረጎሙት አምስቱን የሕግ መጽሐፍት ብቻ ነው የሚለውን ሃሳብ ይህ ጥንታዊ አባት እንደማይቀበለው ነው። እሱም ብቻ አይደለም ይልቁንም ከላይ እንዳየነው ሰማዕቱም ዮስቲንም አይቀበለውም። ሌሎቹም የብሉይ መጽሐፍት በራሳቸው እንደተተረጎሙ በ First Apology: chap. 31 ላይም ገልጾታል

[35] "በግብጽ" ያለው የግሪኩ መጽሐፍ አስቀድሞ በበጥሊሞስ ትእዛዝ በግብጽ ስለተተረጎመ ነው።

[36] Ibid no. 3

“ሃዋርያት ጥንታውያን በመሆን አሁን ላይ ከተነሱ ሁሉ ምንፍቅና ቀድመው የነበሩት እነርሱ **አስቀድመን ከተናገርነው ትርጓሜ ጋር ይስማማሉ፤ ትርጓሜውም ደግሞ ከሃዋርያት ትውፊት ጋር ይተባበራል።** ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ማቴውስ፤ ጳውሎስ እንዲሁም ሌሎቹም፣ ተከታዮቻቸውም ትንቢታዊ ነገሮችን ሲሰጡን ሰባው ሊቃናት እንደተረጎሙት ነው።”

ከዚህ አንጻር የሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ ለቤተ ክርስቲያን ሃዋርያዊ ትውፊት(Apostolic

Tradition) ነው ማለት ይቻላል። ለምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል “ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ። *መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም* ***ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ***”(ዕብ 10፡5) በማለት ይናገራል። ይህንን ቃል የሚናገረው ከመዝሙር 40፡6 በመውሰድ ሲሆን፡ “*ሥጋን አዘጋጀህልኝ*” የሚለው ሃረግ ግን የዕብራይስጡ መጽሐፍ ላይ አይገኝም። የሚገኘው ሰብዓ ሊቃናት(Septuagint) ላይ ነው።

ታድያ ግን እንዲህ እንዳለ ሆኖ በዛ ሰዓት የነበረው የእብራይስጥ መጽሐፍ በቅዱስ ጀሮም ጥቅም ላይ ውሎም እናገኘዋለን። ጀሮም በ5ኛው ክ/ዘመን አካባቢ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስን ቀጥታ ከእብራይስጥ ወደ ላቲን ተርጉሞታል ይህም የላቲን ትርጓሜ ቩልጌት(Vulgate) ይባላል። ጀሮም ይህንን የላቲን ትርጓሜ ሲሰራ ከእርሱ በፊት ግን ሌላ የላቲን ትርጓሜ ነበር ቬቱስ ላቲና(vetus latina) የሚባል። ይህ የቀደመው ላቲን ትርጓሜ የብሉይ ኪዳን መጽሐፉ የተተረጎመው ከሰብዓው ሊቃናት ነበር። በኋላ ግን ጀሮም ከጥቂት መጽሐፍት ውጪ ሌሎቹን የብሉይ መጽሐፍት ከእብራይስጥ ወደ ላቲን ድጋሜ ተረጎመው።ታድያ ግን እርሱ በነበረበት ሰዓት የነበረው አውግስጢኖስ ለጀሮም በላካቸው ደብዳቤዎች ውስጥ ትልቅ ስልጣን ያለው ሰብዓ ሊቃናቱ እንደሆነና ከእብራይስጥ ለምን መተርጎም እንዳስፈለገው ሲጠይቀው እንመለከታለን። ሁሉም አባቶች በሚባል ደረጃ ሲጠቅሱ የሚጠቅሱት ከሰብዓ ሊቃናቱ ግሪክ ነበር። ያም ሆነ ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ ክብር የነበረው ከእብራይስጡ ይልቅ ግሪኩ እንደነበር ግልጽ ነው። ምናልባት ተጨማሪ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ጥንታዊ በ4ኛውና 5ኛው ክ/ዘመናት ላይ በእጅ የተጻፉ እደክታባት(Manuscripts) ስንመለከት የብሉይ መጽሐፋቸው ግሪክ ሰብዓ ሊቃናት ናቸው። ከእነዚህም ጥንታውያን እደክታባት እነ ኮዴክስ ሳይናይቲከስ(codex sinaiticus)፣ ኮዴክስ ቫቲካነስ(codex vaticanus) እና ኮዴክስ አሌክሳንድሪነስ(codex alexandrinus) ይጠቀሳሉ።

## ማሶሬቲክ ቴክስት(Masoretic Text) እና ሰብዓ ሊቃናት (ልዩነት)

ይህ ደግሞ የእብራይስጥ መጽሐፍ ሲሆን የማሶሬት ቡድን በሚባሉ አይሁዳውያን ከ7ኛው እስከ 11ኛው ክ/ዘመን ባለው አካባቢ ውስጥ የተጻፉ እደክታባት ስብስብ እንደሆነ ይነገራል።[37] ይህ የእብራይስጥ መጽሐፍ ምንም እንኳን ቋንቋውን እብራይስጥ ብንልም ከላይ ስንናገርለት ከነበረው አስቀድሞ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ከተጻፈበት የእብራይስጥ ቋንቋ ጋር ግን ልዩነት ነው። ስለዚህም በስመ እብራይስጥ የቀደመው የእብራይስጥ መጽሐፍ መስሎ ሊታየን አይገባም። ይህ መጽሐፍ አሁን ላይ አይሁዳውያን የሚቀበሉት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው። ታናክ(Tanakh) ይሉታል። ይህም በውስጡ ከያዛቸው ሦስት ክፍሎች አንጻር ነው: Torah(የሕግ መጽሐፍት), Neviim(የነቢያት መጽሐፍት) እና Ketuvim(ጽሑፎች)። ከጌታ መምጣት በኋላ አይሁዳውያን ብዙ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ቆርጠው አስወጥተዋልና በእነርሱ አቆጣጠር በውስጡ 24 መጽሐፍትን የያዘ ነው። የፕሮቴስታንቱም መጽሐፍት የሚተረጎሙት ከዚሁ ጽሑፍ ሲሆን ይህም የሆነው ከማርቲን ሉተር መነሳት ጀምሮ እንጂ ከዛ በፊት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በካቶሊኩም በኦርቶዶክሱም ይህ የማሶሬቶች ጽሑፍ ተቀባይነት አልነበረውም። ይህም የሆነበት ምክኒያት አስቀድሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን ነገር ሁሉ ከመቃወም የመነጨ ነው። አንዳንድ ብዙም ያላነበቡ ፕሮቴስታንት ወንድሞች ከጥያቄ ለማምለጥ ያህል ምንም እንኳን የብሉይ ኪዳን መጽሐፋቸው ከሰብዓው ሊቃናትም እንደሚተረጎም ቢናገሩም እውነታው ግን አሁን ላይ ከሚገኘው በ1008ዓም ገደማ ከተቀዳ ኮዴክስ ሌኒንጋርድ ከተባለ የማሶሬቲክ ቴክስት እደክታብ ብቻ እደሆነና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከዚህ እደክታብ በእድሜ ቀደም ከሚል ግን ደግሞ ብዙ መጽሐፍቶቹ ከጠፉበትም ኮዴክስ አሌፖ የማሶሬቲክ ቴክስት እንደሚተረጎም የራሳቸውም ሊቃውንት ይመሰክራሉ።[38] የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ቁጥርም ላይ በፕሮቴስታንቱና በሌሎቹ መካከል ልዩነት የተፈጠረው በሰብዓ ሊቃናት እና በማሶሬቲክ ቴክስት መካከል ልዩነት በመኖሩ ምክኒያት ነው። ታድያ ይህ የአዲሶቹ አይሁድ መጽሐፍ እንዲሁም የፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ መሰረት የሆነው የማሶሬቶች ጽሑፍ ምንም እንኳን ለማነጻጸሪያነትና ለማጥናትያህል ልንጠቀምበት ብንችልም ከሰብዓ

---

[37] Emmanuel tov: textual criticism of the Hebrew bible, 2nd ed. Pg 22

[38] THE DEAD SEA SCROLLS BIBLE translated by MARTIN ABEGG, JR., PETER FLINT, AND EUGENE ULRICH, pg 9

ሊቃናቱ ጋር በተዓማኒነት ሊስተካከል አይችልም።በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጠብቆ የኖረ አይደለምና የመንፈስ ቅዱስ ጠብቆትም አይኖረውም። በዚህም ምክኒያት ብዙ እንከኖች ያሉበት የተበረዘ መጽሐፍ ሆኗል። ይህንንም አንዳንድ ነገሮችን እያነሳን በንጽጽር መልክ ለማየት እንሞክራለን።

የመጀመሪያው ከላይም እንዳነሳነው ይህ ጽሑፍ በአዲሱ እብራይስጥ የተጻፈ በኋላ ዘመን የመጣ ነው። በዚህም ምክኒያት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን የጻፉት ቅዱሳን ሰዎች ይህንን መጽሐፍ ቢያዩት ሊያነቡት እንኳን አይችሉም ምክኒያቱም ሌላ እብራይስጥ ስለሆነ። ይህንን ያልነው ከላይም እንደተናገርነው በስመ እብራይስጥ ትልቅ ግምት እንኳን እንዳይሰጠው ነው። ባይሆን ግን ይህንን አዲስ ጽሑፍ የተወሰነ ስንመለከተው ከኦሪጅናል ዕብራይስጥ ከታቡ ጋር ቀርቶ ከላይ ከሰብዓ ሊቃናቱ ጋር ስናነጻጽር ከነበረው እብራይስጥ ጋርም ልዩነት አለው። ይህንንም ለምሳሌ በቁምራን ከተገኙ የእብራይስጥ መጽሐፍት ጥቅሎች እና ጀሮም እርሱ በነበረበት ጊዜ ከእብራይስጡ ከተረጎመው የላቲን መጽሐፍ ጋር በማነጻጸር ማየት የሚቻል ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ሐዲስ ኪዳንን እስትንፋሰ እግዚአብሔር ነው ብሎ ለሚያምን ሰው በሐዲስ ኪዳን ላይ ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሱ ጥቅሶችን ሄዶ መፈተሽ የግድ ይለዋልና የተጠቀሱ ጥቅሶችን እየያዝን የብሉይ ኪዳን አቻቸውን ከሰብዓ ሊቃናት እና ከማሶሬቲክ ጋር እናመሳስለዋለን።

| የሐዲስ ኪዳን ጥቅስ | ሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ | ማሶሬቲክ ጽሑፍ(የፕሮቴስታንቱ) |
|---|---|---|
| እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች..<br>(ማቴ 1፡23) | እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች..<br>(ኢሳ 7፡14) | እነሆ ወጣት ሴት[39] ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች.. |
| ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ<br>(ዕብ 10፡5) | መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ<br>(መዝ 40፡6) | መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ጆሮዎቼን ከፈትክልኝ[40]<br>(መዝ 40፡6(7))<br><br>Sacrifice and offering You did not desire; My ears You have opened<br>(NKJV) |

[39] እዚህ ላይ የፕሮቴስታንቶች መጽሐፍትም እንደ እኛው "ድንግል" ብለውታል። ይህ ግን ከሚተረጉሙበት የእብራይስጥ መጽሐፍ ላይ ያገኙት አይደለም። ይልቁንም ከሰብዓ ሊቃናት ላይ የተኮረጀ ነው ማለት ይቻላል። በዚህም ምክኒያት የእነሱ መጽሐፍ የተበረዘ እንደሆነ እነርሱም ምስክር እየሆኑን ነው ማለት ይቻላል። በእብራይስጡ ስላለው ስለ ትክክለኛው ቃል ግን አይሁዶች በኢንግሊዘኛውም ትርጓሜያቸውም ላይ "Young Woman" ነው ያሉት(JPS Hebrew-english tanakh)። ፕሮቴስታንቶች ስለ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ መናገር ያለባቸው አይሁዶች እንደሆኑ ያስባሉ ግን ደግሞ መልሰው የአይሁዳውያኑን ወደ ጎን ሲያደርጉ እናያለን።

[40] እዚህ ጥቅስ ላይ ደግሞ እኛ ሃገር ያለው የፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ ከራሱ ከሚተረጎምበት ከእብራይስጡ ብቻ ሳይሆን በውጭ ካሉት የኢንግሊዘኛ የፕሮቴስታንት መጽሐፍቶችም ሳይቀር ተለይቶ ያው ከእኛው ተወስዶ መጽሐፋቸው ውስጥ "ሥጋን አዘጋጀህልኝ" የሚለው ተካትቷል። ይሄ ማለት የእብራይስጡ ላይ "ጆሮዎቼን ከፈትክልኝ" የሚለው ቃል እስትንፋሰ እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው..?? ያው የእብራይስጡ መጽሐፍ ለመበረዙ እነሱ ራሳቸው ማስረጃ ይሆኑናል። ከቃሉ ጋር በተያያዘ ግን ጠቅላላ የኢንግሊዘኛ መጽሐፍቶች እንደ ማሶሬቲክ ጽሑፉ ነው የሚያስነብቡ ሲሆን እንዲህ ይላል፡ "..My ears You have opened"(NKJV)

| | | |
|---|---|---|
| "..ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ.. ልኮኛል" (ሉቃ 4፡19)[41] | ..ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና [..] ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ.. ልኮኛል (ኢሳ 61፡1) | ..ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና [..] ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ.. ልኮኛል (ኢሳ 61፡1)[42] |
| በነቢዩ በኢሳይያስ የተባለው ይፈጸም ዘንድ እንዲህ ሲል.. አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ። (ማቴ 12፡17፣21) | አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ። (ኢሳ 42፡4) | ደሴቶችም ሕጉን ይጠባበቃሉ (ኢሳ 42፡4)[43] |
| የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ(ለኢየሱስ) ይስገዱ **ይላል**። (ዕብ 1፡6) | የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይሰግዱለታል። (ዘዳ 32፡43) | [ስለዚህ ጉዳይ ምንም አይልም][44] |

[41] እዚህ የሉቃስ ወንጌል ላይ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ የኢሳያስ መጽሐፍ ተሰጥቶት እርሱ ራሱ ያነበበው መጽሐፍ ነው።

[42] እዚህ ላይ ደግሞ ጌታ ካነበበው ከኢሳያስ መጽሐፍ ጋር የፕሮቴስታንቱ ልዩነት አለው። በጌታ ከተደረጉ ተዓምራት ውስጥ የዓይንን ብርሃን መመለስ ነበር። ይህም አስቀድሞ በትንቢት የተነገረ ሲሆንና ራሱ ክርስቶስም በምድር ላይ ሳለ ካነበበው መጽሐፍ ውስጥ የተገኘ ሲሆን የፕሮቴስታንቱ ላይ ግን ይህ ትንቢት የለም። ያው በአንድም በሌላም ምክኒያት ከመጽሐፍ ውስጥ ወጥቷል።

[43] እዚህ ላይም አሕዛብ ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም እንደሚያምኑ የተነገረበትን ትንቢት በሐዲስ ኪዳንም ተጠቅሶ ስናነበው ማሶሬቲክ ቴክስት ላይ ግን ሃሳቡም አልሰፈረም በቦታው። ታድያ ግን እንደተለመደው እዚህ ጋርም ምንም እንኳን ሌሎች ኢንግሊዘኛ ትርጉሞች እንደ ማሶሬቲኩ ቴክስት ቢተረጉሙም የእኛ ሃገሩ ላይ ግን ከእኛው ላይ ተወስዶ ተካቷል። በዚህም የማሶሬቲክ ጽሑፍ ተዓማኒነት እንደሌለው ይገልጹልናል። የኢንግሊዘኛው እንዲህ ይላል፡ "and the isles shall wait for his law"(KJV)

[44] እዚህ ላይ ምንም እንኳን ጳውሎስ የጠቀሰው ጥቅስ ማሶሬቲክ ቴክስት ላይ ጭራሹኑ ባይገኝም ከዚህ በተሻለ የሚያስገርመን ግን ይህ የጳውሎስ ጥቅስ በሙት ባህር ከተገኙ የእብራይስጥ ጥቅሎች ውስጥ ዘዳግም 32፡43 ከሰብዓ ሊቃናቱ እና ከጳውሎስ ጋር ይስማማል። ይህ ማሶሬቲክ ቴክስት ግን ከጥንታውያን እብራይስጥ ጋርም ልዩነቱ ጉልህ ሆኖ የታየበት ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ዮሴፍም አባቱን ያዕቆብንና ሰባ አምስት ነፍስ የነበረውን ቤተ ዘመድ ሁሉ ልኮ አስጠራ። (ሃዋ 7፡14) | ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብፅ የገቡት የያዕቆብ ቤተ ሰዎች ሁሉ ሰባ አምስት ናቸው። (ዘፍ 46፡27) | ወደ ግብፅ የገቡት የያዕቆብ ቤተ ሰዎች ሁሉ ሰባ ናቸው። (ዘፍ 46፡27)[45] |
| ደግሞም ኢሳይያስ። "የእሴይ ሥር አሕዛብንም ሊገዛ የሚነሣው ይሆናል፤ በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ" ይላል። (ሮሜ 15፡12) | የእሴይ ሥር አሕዛብንም ሊገዛ የሚነሣው ይሆናል፤ በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ። (ኢሳ 11፡10) | ለአሕዛብ ምልክት ሊሆን የቆመውን የእሴይን ሥር አሕዛብ ይፈልጉታል (ኢሳ 11፡10) |
| የሠራችኋቸውን ምስሎች እነርሱንም የሞሎክን ድንኳንና ሬምፋም የሚሉትን የአምላካችሁን ኮከብ አነሣችሁ..ተብሎ እንዲህ ተጽፎአል (ሃዋ 7፡43) | ለራሳችሁም የሠራችኋቸውን ምስሎች፥ የሞሎክን ድንኳንና የአምላካችሁን የሬፋን ኮከብ አነሣችሁ። (አሞ 5፡26) | ለራሳችሁም የሠራችኋቸውን ጣኦታት ቺኡንን ንጉሳችሁን ሲኩትን የአማልክቶቻችሁንም ኮከብ አነሣችሁ። (አሞ 5፡26)[46] |

[45] "ጸጋና ኃይል የተሞላ" ተብሎ የተመሰከረለት እስጢፋኖስ በብዙ የአይሁድ ሊቃውንት ፊት ወደ ግብጽ ስለ ገቡት የያዕቆብ ቤተ ሰዎች ብዛት ሰባ አምስት እንደሆኑ ሲናገር የሰብዓ ሊቃናቱም ትርጓሜ ይስማማል። የማሶሬቲኩ ግን ሰባ ይላል። በእርግጥ ይሄ የቁጥር ልዩነት እንደ ትልቅ ግጭት ባናየውም ግን ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ሲያነበው ሐዋርያት ሲጠቀሙበት የነበረውን መጽሐፍ የትኛው እንደሆነ እንድናውቅበት ይረዳናል።

[46] እዚህ ጋርም እንደምንመለከተው እስጢፋኖስ ጠቅሶ ከተናገረበት መጽሐፍ አሁን ላይ የፕሮቴስታንቱ መጽሐፍ ልዩ ነው። ያው እንደተለመደው እኛ ሃገር ያለው መጽሃፋቸው ላይ ግን ማሶሬቲክ ቴክስትን ገፍተር አድርገው ከሰብዓ ሊቃናቱ አስፍረውበታል። የኢንግሊዘኞቹ መጽሐፍት ግን አብዛኛው ከላይ ካስቀመጥነው ከማሶሬቲክ ቴክስቱ ጋር አንድ ነው። ለምሳሌ እንዲህ ይላል እኛ የወሰድንበት የኢንግሊዘኛ መጽሐፍ፡ "You also carried Sikkuth your king And Chiun, your idols, The star of your gods, Which you made for yourselves." (NKJV) ይሄ ቦታ ላይ በጀሮም ሰዓት በዛ ሰዓት ከነበረው እብራይስጥ የተተረጎመው ላቲኑ ላይም ወደ ሰብዓ ሊቃናቱ በጣም የተጠጋ ሲሆን ከማሶሬቲክ ቴክስት ጋር ፍጹም ይለያል። ይህ የሚያሳየን ከላይ እንዳልነውም ማሶሬቲክ ቴክስት እነ ጀሮም በነበሩበት ሰዓት ከነበረውም እብራይስጥ መጽሐፍም ይለያል።

| | | |
|---|---|---|
| በሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ እነ ሙሴ የተሻገሩት ባህር "ቀይ ባሕር( ερυθρά θάλασσα)" እንደሆነ ተቀምጧል። አንዳንድ ቦታ ላይ "ኤርትራ ባህር" ቢባል "ቀይ" የሚለውን ቃል የሚተካውን የግሪኩን ቃል ερυθρά(ኤሩትራ) ቀጥታ ቃሉን ሳይተረጉሙ ከግሪኩ በመውሰድ እንደሆነ ልብ ልንለው ይገባል።<br><br>(ሐዋ 7፡36፣ ዕብ 11፡29) | በግሪኩ ብሉይ ኪዳን ላይ ቀይ ባህርን "ቀይ ባህር" ይለዋል። ስለዚህም ቀይ ባህርን ቅዱስ እስጢፋኖስም ቅዱስ ጳውሎስም ያውቁታል። ምክኒያቱም የእኛ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እና የሐዋርያት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ተመሳሳይ ነው። | የዕብራይስጡ መጽሐፍ "ቀይ ባህር" የሚባል ነገር አያውቅም። ብዙዎቹ ከዚሁ የሚተረጎሙ መጽሐፍት "Red sea"(ቀይ ባህር) በማለት ቢያስቀምጡም ዕብራይስጡ ግን "reed sea"(ሸንበቆ የሚበቅልበት ባህር) ይለዋል። የዕብራይስጡን ወደጎን አድርገው ከእኛው ከሰብዓ ሊቃናት ላይ መተርጎማቸው መጽሐፋቸው የተበረዘና ብዙ ስህተቶችን የያዘ እንደሆነ እየመሰከሩልን ይመስላል።<br><br>ስለዚህም የሐዋርያቱ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እና የፕሮቴስታንቱ ወይም አሁን ያሉ የአይሁዳውያኑ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ይለያያል ማለት ነው። |

## <u>የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ቀኖና</u>

ቀኖና(canon) ማለት መለኪያ መመዘኛ እንደማለት ነው። አሁን ባለንበት ጊዜ ቀኖና ብለን ስንናገር የእግዚአብሔር ቃል የሆኑትን መጽሐፍት ካልሆኑት መለየታችን ቢሆንም ከጥንት ጀምሮ ግን የመጽሐፍት ቀኖና ሲባል ግዴታ እንዲህ ማለት አይደለም። ይልቁንም የእግዚአብሔር ቃል በሆኑት መጽሐፍትም መካከል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነበቡ ተብሎ በቀኖና ሊለዩ ይችላል። ይህንን ምናልባት ወደታች ግልጽ የምናደርገው ይሆናል። የብሉይ ኪዳን ቀኖና በአይሁድም ዘንድ ሆነ በክርስቲያኖች በተለያዩ አካባቢዎችና ሰዎች ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶች የሚሰጡበት ነገር ነበር። ቀኖና በማድረግ ደረጃ አይሁዳውያን የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍት ወስነው አያውቁም። ከጌታችን ክርስቶስ መምጣት በኋላና ከክርስቲያኖች መነሳት በኋላ ግን በተለይ የክርስቲያኖችን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት መጠቀም ጋር ተያይዞ ይሄንን አንቀበልም ያንን አንቀበልም የሚሉ ሃሳቦች ተነሱ። ከዛም በኋላ ያለምንም ትልቅ ማስረጃ 24 መጽሐፍት እንዳሉ ማወጅ ጀመሩ። ሻዬ ኮኸን(cohen, shaye) የተባለ የአይሁድ መምህር(Rabbi) እና የታሪክ ምሁር በእውቅ መጽሐፉ ላይ እንዲህ አለ፡ "አጠቃላይ የታናክ(tanakh) የቀኖና ሂደት 'ለምን እነዚህ መጽሐፍት ተካተቱ እነዚያስ ለምን አልተካተቱም?' የሚል ጥያቄን ያስነሳል።

መክብብ ተካትቶ ለምን ሲራክ አልተካተተም? መጽሐፈ አስቴር ተካትቶ ለምን መጽሐፈ ዮዲት አልተካተተም? ዳንኤል ተካትቶ ለምን ሄኖክ አልተካተተም? እነዚህ በቀኖና ውስጥ የተካተቱትን መጽሐፍት ካልተካተቱት የሚለይ ተጨባጭና እርግጥ የሆነ መመዘኛ የለም።"[47] በማለት ከተናገረ በኋላ፡ "ስለምን ጦቢትን፣ ሲራክን እና ዮዲትን አልተቀበልንም?" በማለት ይጠይቅና "አናውቅም" በማለት ይመልሳል።[48]

ይኸው የአይሁድ ምሁር እንደተናገረው "የመጽሐፍ ቅዱስን "ቀኖና" የሚወስኑት የተወሰኑ የተማሩት(ምሁራኑ) ሳይሆኑ የአይሁድ ማህበረሰቡ(communities) ናቸው። መጽሐፉ ተቀባይነት እንዲኖረው በአይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ግድ ነው። የተለያዩ ማሕበረሰቦች ደግሞ የተለያየ ቀኖናን ይቀበላሉ። የጆሴፈስ እና የራቢዎቹ ቀኖና አጭሩ ቀኖና ሲሆን[49] የኩምራኖቹ አይሁዳውያን መጽሐፍ እና በውጭ ያሉ አይሁዳውያን(the diasporas) መጽሐፍ ቁጥሩ የሚበልጥ ነበር።"[50]

በዚህ በራሳቸው የአይሁድ ምሁር መሰረት ከክርስቶስ መምጣት በፊት የነበሩት በቁምራን አካባቢ ይኖሩ የነበሩ የአይሁድ ማሕበረሰብ እና በውጭ የነበሩት የአይሁድ ማሕበረሰቦች የሚቀበሉት የመጽሐፍ ብዛት ብዙ እንደነበረ ግልጽ ነው። የክርስቲያኖችም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ከእነዚሁ አይሁዶች የመጣ ሲሆን ክርስቶስ አምላካችን ከመጣ በኋላ አይሁዳውያን የራሳቸውን መጽሐፍት ከደው ወይም ደግሞ ምናልባትም የጥቂት አይሁዳውያን ብቻ ተቀባይነት የነበረውን ቀኖና በመያዝ ሌሎች እስትንፋሰ አምላክ የሆኑትን መጽሐፍት ጥለዋል።

በክርስትናም ዘንድ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ጉዳይ አጨቃጫቂ ነበር። የተለያዩ አመለካከቶችም በተለያዩ አባቶች ሲሰጡ ነበር። እጅግ ጥቂት የሚባሉ አባቶች ቀጥታ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ የተነሱ አይሁዶችን መጽሐፍት ቁጥር በመያዝ አንዳንድ መጽሐፍትን ከቀኖና ውጭ ሲያደርጉ ነበር ምንም እንኳን አሁን ላይ ካሉ አይሁዳውያንና ፕሮቴስታንቶች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰል ባይሆንም። ታድያ ግን በዋናነት ተቀባይነት የሚኖረው አጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ በብዙዎች ይታመን የነበረውና በትውፊት የመጣው እንጂ በግለሰብ ደረጃ የተሰጡ ሁሉ ተቀባይነት አላቸው ማለት

---

[47] Cohen, Shaye: From The Maccabees to The Mishnah 2nd ed: pg 182
[48] Ibid, pg 183
[49] እነ ጆሴፈስ ከክርስቶስ መምጣት በኋላ የተነሱ ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ከክርስቶስ መምጣት በፊት የነበሩ እንደሆኑ ልብ ልንለው ይገባል።
[50] ibid pg 184

አይደለም። እንደዛ ቢሆን ኖሮ በብሉይ ኪዳን ላይ ብቻ ሳይሆን በሐዲስ ኪዳን ላይም ብዙ ልንጥላቸውና ልንጨምራቸው የምንችላቸው መጽሐፍት በኖሩ ነበር። ስለ ቀኖና ስናወራ ኮኸን ሻዬም እንደሚለው "ቀኖና ሂደታዊ እንጂ ክስተት አይደለም"( Canonization is a process, not an event)። በእርግጥ ጥንታዊ በሚባሉ አብያተ ክርስትያናት(በካቶሊክ፣ በምስራቅ ኦርቶዶክስ፣ በኦሬንታል ኦርቶዶክስ) መካከልም የቀኖና ልዩነት አለ። ታድያ ግን አንድ አስተውለን ማለፍ የሚገባን ነገር የመጽሐፍት ብዛት ወይም ቁጥር ዶግማ አይደለም። አብያተ ክርስቲያናትንም የሚለያይ ነገር አይደለም። ያው ሌላ ዶግማ የሚሰብክ በቅዱሳን ስም የተሰየሙ የመናፍቃንን መጽሐፍት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስካላካተቱ ድረስ ማለት ነው። ይህንን ደግሞ የሚያደርግ አንድም ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን የለም። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ላይ ፕሮቴስታንቱ 39 መጽሐፍትን ሲቀበሉ ካቶሊክ 46 መጽሐፍትን ትቀበላለች፣ የግሪክ ኦርቶዶክስ 49 ትቀበላለች የኛ ቤተክርስቲያን ደግሞ 46 ትቀበላች፤ በመካከላቸው ግን የመጽሐፍት አቆጣጠር ልዩነት አለ። በቤተ ክርስቲያናችን የብሉይ ኪዳን ቀኖና(የእግዚአብሔር ቃል) ውስጥ የሚካተቱትን ተመልክተን እዚህ ጋር እንዘርዝርና ከጥንት ጀምሮ የመጣውን ቀኖና ለመመልከት እንሞክራለን።

በዚህ ዝርዝር ውስጥ በደማቅ ያስቀመጥኳቸው በፕሮቴስታንቱ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውን ሲሆን አያይዤ ከሰብዓ ሊቃናት የተወረሰውን የኢንግሊዘኛ ስሞቻቸውንም አስቀምጣለሁ።

1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት
3. ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ኦሪት ዘኍልቁ
5. ኦሪት ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት

8. መጽሐፈ ሩት

9. መጽሐፈ ሳሙኤል 1 እና 2

10. መጽሐፈ ነገስት 1 እና 2

11. መጽሐፈ ዜና መዋዕል 1

12. መጽሐፈ ዜና መዋዕል 2

13. መጽሐፈ ኩፋሌ( Jubilees)

14. መጽሐፈ ሄኖክ(Enoch: ከላይ ለኩፋሌ ያስቀመጥነውን ሪፈረንስ ተመልከት)

15. መጽሐፈ ዕዝራ እና ነህምያ

16. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል እና ዕዝራ 2(first and second Esdras)

17. መጽሐፈ ጦቢት(Tobit)

18. መጽሐፈ ዮዲት(Judith)

19. መጽሐፈ አስቴር

20. መጽሐፈ መቃብያን 1(Maccabees 1)

21. መጽሐፈ መቃብያን 2 እና 3(Maccabees 2 and 3)

22. መጽሐፈ እዮብ

23. መዝሙረ ዳዊት

24. መጽሐፈ ምሳሌ(እስከ ምዕራፍ 24 ድረስ ብቻ)

25. መጽሐፈ ተግሣጽ(ይህ ሌላ መጽሐፍ አይደለም፤ ከመጽሐፈ ምሳሌ የቀሩትን ምዕራፋት የያዘ ነው።)

26. መጽሐፈ ጥበብ(Wisdom)

27. መጽሐፈ መከብብ

28. መሓልየ መሓልይ

29. መጽሐፈ ሲራክ(Sirach)

30. ትንቢተ ኢሳያስ

31. ትንቢተ ኤርምያስ ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ ፣ ተረፈ ኤርምያስ እና ባሮክ(Letter of jeremiah and Baruch)

32. ትንቢተ ሕዝቅኤል

33. ትንቢተ ዳንኤል

34. ትንቢተ ሆሴ

35. ትንቢተ አሞጽ

36. ትንቢተ ሚክያስ

37. ትንቢተ ኢዩኤል

38. ትንቢተ አብድዩ

39. ትንቢተ ዮናስ

40. ትንቢተ ናሆም

41. ትንቢተ ዕንባቆም

42. ትንቢተ ሶፎንያስ

43. ትንቢተ ሃጌ

44. ትንቢተ ዘካርያስ

45. ትንቢተ ሚልክያስ

46. [……………] ተካትቶ አልታተመም

እኚህን መጽሐፍት በቤተ ክርስቲያናችን በትውፊት ተቀበልን። በጥንታዊ ማስረጃዎች ከፕሮቴስታንቱ ጋር ያለንን ልዩነት ለማየት እንሞክራለን፡

## <u>ፕሮቴስታንቱ ለማይቀበሏቸው መጽሐፍት ጥንታዊ ማስረጃዎች</u>

1. **የሙት ባህር ጥቅሎች(dead sea scrolls):** የሙት ባህር ጥቅሎች ሲባል መስማት ያው የተለመደ ነው። እንግዲህ በ1940ዎቹ አካባቢ የተገኘው ይህ ግኝት ላይ የተወሰነ ግንዛቤ እንዲኖረን አንዳንደ ነገሮችን እናንሳ፡ አስቀድመን ስለ ግኝቱ ስናነሳ እንዳልነው በ1940ዎቹ

ውስጥ በሙት ባህር ዳርቻ ከቤዱኢን ጎሳ የሆነ አንድ እረኛ ፍየሉ ትጠፋበትና እሷን በሚያፈላልግበት ወቅት ወደ ዋሻ ውስጥ እንደገባችበት በመረዳት ወደዛ ዋሻ ቀርቦ ፍየሏ ትወጣ ዘንድ ወደ ዋሻ ውስጥ ዲንጋይ ይወረውራል። በዚህ ሰዓት ግን ይህ እረኛ ባልጠበቀው መልኩ በወረወረው ዲንጋይ ሸክላ ሲሰበር ይሰማና ገብቶ ለመመልከት ይሞክራል በዚህ ሸክላ ውስጥም የነበረው ጥንታዊ ጥቅሎች ነበር። ከዚህ በኋላብ እኚህ ጥቅሎች ይህ ጎሳ ይኖርበት በነበረበት አካባቢ በተለይም ከ1947ዓም ጀምሮ ገበያ ላይም መቅረብ ጀመሩ። የእነዚህ ጥቅሎች ጉዳይም በሌሎች አለማት ላይም ተሰማ። ታሪኩን ለማሳጠር ያህል በዚህ እረኛ የተጀመረው ይህ ግኝት በዛ ቦታ ላይ ሌሎችም ጥቅሎች ሊኖሩ እንደሚችሉ በማሰብ በአርኪዮሎጂስቶች ምርምር ተደረገበት ምርምሩም አጥጋቢ ነበር አሥር ዋሻዎች የተገኙ ሲሆን እያንዳንዳቸው ውስጥ ብዙ ጥቅሎች ተገኝተዋል።

ከእነዚህም ጥቅሎች 4ኛው ዋሻ ውስጥ የተገኙት ብዙውን ቁጥር ይይዛሉ። ከእነዚህ ከተገኙት አጠቃላይ ወደ 930 ከሚሆኑ ጽሑፎች ውስጥ ከ25 ፐርሰንት በላዩ ቅዱሳት መጽሐፍት ናቸው። እነዚህም ጽሑፎች ከ200 ዓመት ቅ.ል.ክ እስከ 100ዓም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጻፉ እንደሆኑ ተመራማሪዎቹ ይገልጻሉ። እነዚህ መጽሐፍት በእነማን ተጻፉ ወይም ደግሞ በእነማን ተይዘው እንደነበረ ማወቁ ደግሞ ለምናነሳው ሃሳብ ጠቃሚ ነውና ስለ እነዚህ ሰዎች እናንሳ፡

**ኤሴይ(**essenes**):** ጆሴፈስ የተባለው በመጀመሪያው ክ/ዘመን የነበረው አይሁዳዊ የታሪክ ጸሐፊ በአይሁዶች ዘንድ ሦስት ክፍሎች እንደነበሩና እኚህም ደግሞ ሰዱቃውያኑ ፣ ፈሪሳውያኑ እና ኤሴይዎች እንደሆኑ ይናገራል። ታድያ ግን ከእነዚህ ሦስት ክፍሎች(Sects) ኤሴይዎች እጅጉን የተለዩ ነበሩ። ሥርዓታቸው ሕይወታቸው ሁሉ ከሌሎቹ ክፍሎች የተለየ እንደነበር ይናገራል። እርስ በእርሳቸው ያላቸው ፍቅር እጅጉን ያስገርም ነበር። በእነርሱ ማሕበር ውስጥ አንዱ ለሌላው የሚሸጠው ወይም ደግሞ ሌላው ከሌላው የሚገዛው ነገር የለም። ምክኒያቱም "የእኔ" የሚባል ነገር በእነርሱ ዘንድ አልነበረም። ሁሉም በሕብረት ነው የሚኖሩት። ይህ ደግሞ የመጀምሪያዎቹን ክርስቲያኖች ኑሮ ያስታውሰናል(ሐዋ 4፡32)። ታድያ እነዚህ ሰዎች በጣም የሚያስገርመው ሃሳባቸው ሁሉ ቅድስና እንጂ ሥጋዊ አምሮቶች አልነበሩም። ጆሴፈስም በመገረም እንዲህ ይላል፡ "ለእግዚአብሔር ያላቸው ቅድስና ፍጹም ያልተለመደ ነው ፤ ጸሃይ ከመውጣቷ በፊት ምንም ዓይነት ዓለማዊ የማይጠቅም ወሬን አይናገሩም ፤ ይልቁንም ከአባቶቻቸው የተቀበሉትን ጸሎት ያደርጋሉ። ጸሃይ ከወጣች በኋላም ሁሉም ወደ ሥራ

ይወጣል እስከ 11 ሰዓትም ጸሃይ እስክትጠልቅ ይሰራሉ። በቀዝቃዛ ውኃ ታጥበው ነጭ ከለበሱ በኋላ ሁሉም በሕብረት ሆነው በአንድ ቤት ውስጥ እራትን ይመገባሉ። ሌሎች የአይሁድ ክፍሎች እንኳን በዚህ ቦታ ላይ አይቀላቀሉም። ልክ በቅዱስ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንዳለ ንጹሕ ስብእና ባለው ሥርዓት ያከናውናሉ" በማለት ይናገራል ጆሴፈስ።[51] ይህ ደግሞ ምናልባትም ካስተዋልነው የክርስቲያኖችን ሥራዓተ ቁርባን የሚመስል ነገር አለው። እነዚህ ሰዎች በቅድስና ውስጥ እንደ መላእከት ሆነው ይኖሩ እንደነበረና ትንቢቶችንም ይናገሩ እንደነበሩ ይነገራል። እንዲሁም ሃሰት በእነርሱ ዘንድ የተጠላ በመሆኑ መሃላም በእነርሱ ዘንድ የተከለከለ ነበር። ይህም ክርስቶስ ጌታችን "አትማሉ" ያለውን ትእዛዙን ያስታውሰናል። ለሌላ ሰው ያላቸው ርህራሄና ምህረት እንዲሁም የዋሕነታቸውና ለሌላው መኖራቸው ያስገርማል። ሕይወታቸው የክርስቲያኖችን ይመስል እንደነበረ ይነገራልም ግልጽም ነውም በእውነት። ይህንን በመያዝ Christian D. Ginsburg የተባሉ አስቀድሞ አይሁድ የነበሩ ጸሐፊ ጌታችን ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ላይ ያነሳቸው ሃሳቦች የእነዚህ የኤሴይዎች መገለጫን እንደሚመስሉ በመናገርና እንዲሁም ክርስቶስ በምድር በተመላለሰበት ወራት ጸሃፍትን ፣ ፈሪሳውያንን እና ሰዱቃውያኑንም እየተቸ ሲናገር ስለ ኤሤዮች ግን ምንም አለማለቱ ክርስቶስ ያስተምር የነበረውን አይነት ሕይወት ለመኖር የሚጥሩ ሰዎች እንደነበሩ ያሳያል በማለት በመናገር የክርስትናን ሕይወት ከኤሤዮች ሕይወትና ትምሕርት ጋር በማነጻጸር ይናገራል። ታድያ ይህ ሰው ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ ከአይሁድ እንደመምጣቱ ሊሆን የሚችለው ከሦስቱ ክፍሎች አንዱ ነውና ከኤሤዮች ሊሆን ይችላል በማለት ይናገራል።[52] ሌላው በጣም የሚያስገርመን ነገር የእግዚአብሔር ልጅን አጥብቀው መጠባበቃቸው ነው። ይህም ለምሳሌ በአራተኛው ዋሻ (cave 4) ከተገኙ ጽሑፎች ውስጥ አንድ የአረማይክ ጽሑፍ ስለሚመጣው መሲሕ "የእግዚአብሔር ልጅ" ፣ "የልዑል ልጅ" በማለት እና ለዘላለምም እንደሚገዛም ይናገራል ይህም በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ላይ መልአኩ እመቤታችንን ሲያበስራት ስለሚወለደው ጌታ ከተናገረው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነገር ነው። እንዲሁም በ11ኛው ዋሻ (cave 11) የተገኘው የመልከጸዴቅ ጥቅል (Melchizedek Scroll) ተብሎ የሚታወቀውም ጥቅል "ይቅር የማለትና ሰይጣንን የመርታት ኃይል ስላለው የእግዚአብሔር

[51] The wars of jews, Bk. 2, chap 8
(ስለ ኤሤይዎች ጆሴፈስ የተናገራቸውን ጠቅላላ እዚሁ ክፍል ላይ የሚገኙ ናቸው)
[52] Christian D. Ginsburg: The essenes: their history and doctrines, pg 24

መሳይ መገለጥ ይናገራል።"[53] አቡነ ጎርጎርዮስ በረከታቸው ይደርብንና ስለ ኤሤዮች እንዲህ አሉ፡ "ኤሤይ የሚባሉት (የአይሁድ) ክፍሎች ከፈሪሳውያኑ የሚለዩት ፈሪሳውያን (መሲሕ ሲመጣ) በጦር ኃይል ነጻ እንወጣለን ሲሉ ፤ ኤሤይ የሚባሉት ደግሞ በተዓምራት በእግዚአብሔር ኃይል ፍልስጤም ነጻ ትወጣለች ብለው ያምኑ ነበር። በቤተልሔም በስተደቡብ ልዩ ስሙ ኩምራን በሚባል ቦታ የሚኖሩ እነዚህ ሰዎች መጽሐፍትን በመጻፍ ጸሎትን በማድረስ ብዙ ጊዜ ቆይተዋል።"[54] በኩምራን አካባቢ ይኖሩ የነበሩ እኚህ ኤሴዮች በዚሁ በኩምራን ዋሻዎች ውስጥ የተገኙ ጥቅሎች ባለቤት እንደሆኑ ይታመናል። ታድያ በ1940ዎቹ ግኝት መሰረት ከእነዚህ አይሁዳውያን ላይ ከተቀበልናቸው መጽሐፍት መካከል አሁን ፕሮቴስታንቱ የማይቀበሏቸውንም ጭምር በመሆኑ ይሄ ግኝት እጅጉን እንዲስበን ያደርገዋል ምክኒያቱም እንደ ማስረጃ እንጠቅሰዋልንና። ከላይ እንደተመለከትነው ኮኸን ሻዬ የተባለው የአይሁድ ራቢና የታሪክ ምሁርም በኩምራኖች(ኤሴዮች) ዘንድ የነበረው የመጽሐፍት ብዛት በኋላ ከተነሱ ከነ ጆሴፈስና ራቢዎች ከፍ ያለ እንደነበረ መግለጹን አይተናል። በዚህ እነርሱ ሲኖሩበት ከነበረው አካባቢ ከተገኙ መጽሐፍቶቻቸው መካከል ደግሞ እነ ሲራክ ፣ ጦቢት ፣ ተረፈ ኤርሚያስ ፣ ሄኖክ እና ኩፋሌን ያካትታል። በተለይ ከዚህ ግኝት በፊት ብዙ ሊቅ ነን ባዮች መጽሐፈ ጦቢትን ከ1ኛው እስከ 3ኛው መቶ ክ/ዘመን ባለው ውስጥ እንደተጻፈ ሲናገሩ ቢቆዩም ይህ ግኝት ግን አፉቸውን አዘግቷል ምክኒያቱም 4Qtobit[55] እደኪታብ ከክርስቶስም መምጣት 100 ዓመት በፊት የተጻፈ ነውና በማለት ወደ ኢንግሊዘኛ በእውቅ ሊቃውንት የተተረጎመው የሙት ባህር ጥቅል መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።[56]

2. **ጥንታውያኑ እደ ከታባት**፡ እደ ከታባቱ እጅግ ጥንታዊ ከመሆናቸው የተነሳ የጥንት ቤተክርስቲያን የትኞቹን መጽሐፍት ትቀበል እንደነበረ ትልቅ ማስረጃ ነው።

---

[53] cale Clarke: The Ever-Deepening Mystery of the Dead Sea Scrolls, an internete article

[54] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ገጽ 19

[55] 4Qtobit ይሄ የጥቅል ስም አቀማመጥ ሲሆን የእነዚህ ጥቅሎችም አነባበብ እንዲህ ነው፡ መጀምሪያ ላይ ያለችው "4" 4ኛ ዋሻ ማለት ሲሆን Q ደግሞ Qumran(ኩምራን) ለማለት ነው። ከQ በኋላ ሌላ የሚገባ ቁጥር ሲሆን የጥቅሉን ቁጥር መናገሩ ነው።

[56] THE DEAD SEA SCROLLS BIBLE translated by MARTIN ABEGG, JR., PETER FLINT, AND EUGENE ULRICH, pg 378

codex sinaiticus(ሳይናይቲከስ), codex vaticanus(ቫቲካነስ), codex alexandrinus(አሌክሳንድሪነስ), codex venetus(ቬኔቱስ), Codex Ambrosianus(አምብሮሲያነስ), Codex Sangermanensis(ሳንገርማነሲስ), Codex Amiatinus(አሚያቲነስ),

እኚህና የመሳሰሉት የብሉይ እና ሐዲስ ኪዳንን መጽሐፍት የያዙ እደ ክታባት የተጻፉበት ዘመን በ4ኛውና በ5ኛው መቶ ክ/ዘመን አንዳንዶቹም ከዛ አለፍ ብለው ሲሆን የብሉይ መጽሐፋቸው አሁን ላይ ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውንም መጽሐፍት ያካተቱ ነበር። [57]

እንዲሁም በ6ኛው ክ/ዘመን ተጻፈ የተባለው አንዳንዶች ደግሞ 4ኛው ክ/ዘመን ወይም ከዛም በፊት እንደነበረ የሚናገሩለት ጥንታዊ የግሪክና ላቲን እደክታብ CODEX CLAROMONTANUS(ኮዴክስ ክላሮሞንታኑስ) የጳውሎስን መልእክታትን ብቻ የያዘ ሲሆን መሃል ላይ ግን 4 ገጾች ክፍት ሆነው እዛ ላይ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት በላቲን ስማቸው ተዘርዝረዋል። በዚህም ዝርዝር ውስጥ ፕሮቴስታንቱ የማይቀበሏቸው መጽሐፍት የተካተቱ ነበሩ።[58]

3. **ጥንታውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜያት ይዘት፡** ያው የግሪኩ ትርጓሜ በዋናነት ሲጠቀስ እስካሁንም አይተነዋል። ታድያ ግን እነዚህን በፕሮቴስታንቱ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውን መጽሐፍት ያካተቱ ዛሬም ድረስ ደግሞ የሚያገለግሉ ሌሎችም እጅግ ጥንታውያን ትርጓሜያት አሉ። ለዚህም የጥንቱ ግእዙ እንዲሁም የሲሪያኩ ፔሺታ የቅብጡ(Coptic) ይጠቀሳሉ።

4. **ጉባኤያት፡** በቤተ ክርስቲያን ውስጥ 3 ዓለም ዓቀፋዊ ጉባኤያት እንደተደረጉ ይታወቃል። በእነዚህ ጉባኤያት ላይ ምንም አይነት የመንጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና አልተወሰነም። እነዚህ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት ላይ አባቶች ዶግማ የሆኑ ጉዳዮችን ወስነው ተለያይተዋል። ታድያ ግን በየሃገራቱ ባሉ ሲኖዶሶችም ደግሞ ጉባኤያት ይደረጉ ነበር። በእነዚህ ጉባኤያት ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ጉዳይ ከተነሳባቸው

[57] EDMON L. GALLAGHER and JOHN D. MEADE: The biblical canon lists From early christianity_texts and analysis, chap. 6
[58] Ibid, pg 183

ውስጥ አንስተን ለማየት ያህል የሮሙ ጉባኤ(382ዓም)[59] ፣ የ393ዓም የሂፖ ጉባኤ( Synod at Hippo)[60] ፣ በ419ዓም የተደረገው የካርቴጁ ጉባኤ[61] ላይም የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖናትን እነዚህ ናቸው ብለው ሲያስቀምጡ እንዲሁ በፕሮቴስታንቱ ተቀባይነት የሌላቸውንም ሲያካትቱ እናያለን።

5. **በሐዲስ ኪዳንና በብዙ አባቶችም መጠቀሳቸው፡** ፕሮቴስታንቱ ከተቀበሏቸው መጽሐፍት ውስጥ እንደነ ዕዝራ፣ መኃልየ መኃልይ፣ ሩት፣ አስቴር፣ ዜና መዋዕል፣ መክብብንም ጨምሮ በሐዲስ ኪዳን በጌታም ሆነ በሐዋርያት ያልተጠቀሱ ሲሆኑ ፕሮቴስታንቱ ከማይቀበላቸው ግን ብዙ ሲጠቅሱ እንመለከታለን። እርግጥ ነው በሐዲስ ኪዳን ያልተጠቀሱት መጽሐፍት ትክክለኛ አይደሉም ማለት አይደለም። ግን ደግሞ እነዚህ በፕሮቴስታንቱ ዘንድ ተቀባይነት ከሌላቸው መጽሐፍት ውስጥ በሐዲስ ኪዳን መጽሐፍትም መጠቀሳቸው እንዲሁም በኋላ በተነሱ አባቶችም ተጠቅሰው እንደ ማስረጃ ጥቅም ላይ መዋላቸው አንዱ ሌላው ማስረጃ ነው።

**በሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ለመጠቀሳቸው ጥቂት ማስረጃዎች፡**

A. “**ኑ ጻድቁን እንግደለው**፤ በእኛ ጭንቅና ጽኑዕ ሆኖብናልና፤ ሥራችንንም ይቃወማልና፤ ሕግ በማጣታችንም ያሽሚጥጠናልና፤ የትምሕርታችንንም በደል ይሰብካልና። ‘እግዚአብሔርንም ማወቅ በእኔ አለ’ ይላል። **ራሱንም የእግዚአብሔር ልጅ ያደርጋል** [....] **እግዚአብሔርም አባቱ እንደሆነ ይመካል** [....] **እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆነ ያድነው፤ ከሚቃወሙትም እጅ ይታደገው።**” (ጥበብ 2፡ 12-18)

በእውነት ይህንን ጥቅስ ስናነብ ብሉይ ኪዳንን ሳይሆን ሃዲስ ኪዳንን የምናነብ ነው የሚመስለው። ታላቅ ትንቢት። ጌታ ብዙ ቦታ ላይ ፈሪሳውያኑን ሲወቅስ እናየዋለን። እንዴት የእግዚአብሔርንም ሕግ እንድሚጥሱ እያነሳ ሲናገር አይተናል። በተለይ “ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ያደርጋል” የሚለውን ቃል ይዘን ዮሐ 5፡18 ላይ “እራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከሎ። **እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥**

[59] Tylor Marshall, at www.tylormarshall.com

[60] Karl Josef von Hefele: A Hstory Of The Councils Of The Church: bk.VIII Sec 109

[61] Council of carthage, canon 24: Philip schaf: NPNF s2, vol.14

**ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።**" የሚለውን ቃል ስንመለከት እና "የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆነ ያድነው" የሚለውን ይዘን በማቴ 27፥43 ላይ "የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው።" ብለው የዘበቱበትን ቃል ስናይ ቀጥታ ትንቢቱ እንደተፈጸመ እናያለን። እውን እንዲህ ያለ ትንቢት ሰዎች ከራሳቸው አንስተው ይናገራሉ ወይ..?? ያውም ስለ ጌታ..?? በእውነት መለኮታዊ መጽሐፍ እንደሆነ ግልጽ ነው ብቻ ሳይሆን ይህንን መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ስለ ጌታ የተናገረውን ቃል አለመቀበልና መቃወም በራሱ ምንጩ ከሃሰተኛው መንፈስም ጭምር እንደሆነ ያመለክታል።

B. "የምትወዱኝ ሰዎች ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ ከፍሬዬም ትጠግባላችሁ … **የሚመገቡኝም አይጠግቡኝም፤ የሚጠጡኝም አይሰለቹኝም።** የሚሰማኝም አያፍርም **ለእኔ የሚገዙ** ሰዎች አይስቱም።"

በዚህ ጥቅስ ላይ ደግሞ "ለእኔ ተገዙ" የሚል የሁሉ ገዢ ጌታ በሚያስገርም ሁኔታ ግብዣ ይጠራቸዋል። ኑ ብሉኝ፤ ኑ  ጠጡኝ በማለት። ይሄ በጣም ግልጽ ነው በማቴ 26፥26 ላይ ጌታችን ኢየሱስ እንጀራን ባርኮ ቆርሶ ለሃዋርያት ሲሰጣቸው "ይህ ሥጋዬ ነው" በማለት ሲሆን ጽዋውንም "ይህ ደሜ ነው" በማለት ነበር። በዮሐንስ ወንጌል 6:57 ላይ "**የሚበላኝ** ከእኔ የተነሳ ሕያው ይሆናል" በማለት ቀጥታ ይናገራል። ስለዚህም አስቀድሞ በሰዎች አንደበት ሲናገር የነበረው ጌታ አሁን ደግሞ ቀጥታ በራሱ ተናገረው። ማቴዎስ እንደተናገረ በተራራው ስብከት ትረካ ላይ "ያስተምራቸውም ዘንድ አፉን ከፈተ"። አስቀድሞ የቅዱሳኑን አንደበት የከፈተ አሁን ግን ቀጥታ የራሱን ከፍቶ ተናገረ።

C. በወንጌል ላይ በሙታን ትንሳኤ ዙሪያ ጌታ ሲጠየቅ አንዲት በዘር አለመተካት ምክኒያት ሰባት ወንድማማቾች በየተራ ያገቧት ሴት እንደነበረችና ሁሉም እንደሞቱ ጠቅሰው በኃላ በትንሳኤ የትኛውን እንደምታገባ ይጠይቁታል።(ማቴ 22፥25፤ ማር 12፥20) ታድያ ይህ ታሪክ የተጠቀሰው ከመጽሐፈ ጦቢት ላይ ሲሆን ታሪኩም በምዕራፍ 3 እና 7 ላይ ይገኛል።

D. ሃዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 1፥20 ላይ "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ **ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና**…." በማለት የተናገረው

በመጽሐፈ ጥበብ 9፡1 ላይ ካለው ቃል ጋር የሚዛመድ ነው። ቃሉም እንዲህ ይላል፡ "እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በልቦናቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና ... ***ሥራውንም እያዩ ሰሪውን አላወቁም***"

E. ዮሐንስም በራዕዩ 1፡4 ላይ ሰላምታን ሲያቀርብ "በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት" ይላል። እነዚህ በጌታ ፊት ቆመው የሚያገለግሉ ሰባቱ ሊቃነ መላእክት ናቸው። ይህንንም ቀጥታ የወሰደው ከመጽሐፈ ጦቢት 12፡15 ላይ ሲሆን ቃሉ እንዲህ ይላል፡ "በገናናውና በቅዱሱ ጌትነት ፊት ከሚቆሙ ሰባቱ መላእክት አንዱ መልአክ እኔ ሩፋኤል ነኝ" ይላል። ይህም በሉቃ 1፡19 "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ" ከሚለውና በራዕይ 8፡2 ላይ "በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ" ካለው ጋር ይዛመዳል።

**በአባቶች ለመጠቀሳቸው ጥቂት ማስረጃ**

A. **ቀለሜንጦስ ዘሮም(**25-100ዓም**)፡** "የተባረከችው ዮዲት ከተማዋ በተከበበች ጊዜ ወደ እንግዶች ሰፈር ለመሄድ ከሽማግሌዎች ፈቃድ ጠየቀች፤ ለሃገሯና ሕዝቧ ካላት ፍቅር የተነሳም ራሷን ለአደጋ በማጋለጥ ወጣች፤ ጌታም ሆሎፈርኔሱን በሴት እጅ አሳልፎ ሰጠው።"[62] እንግዲህ የሮሙ ቀለሜንጦስ በስፋት እንደሚታመነው የጳውሎስ ረዳት የነበረው ቀለሜንጦስ(ፊሊ 4፡3) እንደሆነና በሮምም በሃዋርያው ጴጥሮስ እንደተሾመ ይነገራል። ምንም ጥርጥር የሌለው ነገር ግን ከሐዋርያት ከራሳቸው ቀጥታ የተማረ ሰው መሆኑ ላይ ነው። እንግዲህ ይህ የራሳቸው የሐዋርያት ተከታይ ከላይ ያለውን የዮዲትን ታሪክ ከመጽሐፈ ዮዲት ላይ አንስቶ መናገሩ መጽሐፉ በሐዋርያት ዘንድም እስትንፋሰ አምላክ ተብሎ ተቀባይነት ያገኘ ለመሆኑ ምንም አያጠራጥርም።

B. **ሰማዕቱ ዮስቲን(**100-165ዓም**)**፡ ይህ ጥንታዊ ክርስቲያን አባት ከአይሁዱ ሊቅ ከትራፎ(Trypho) ጋር ሲወያይ እንዲህ አለው "ከግብጻዊው በጥሊሞስ ጋር ሆነው ሰባው ሊቃውንት የተረጎሙትን ትርጓሜ ትክክለኛነት አንቀበልም ብለው ሌላን ለማዘገጀት የሞከሩ የአንተ መምህራን ላይ እምነትን ከመጣል የራቅሁ ነኝ፤ ከዚህም ከሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ **ብዙ መጽሐፍቶችን አውጥተው እንደጣሉ**

[62] 1st epistle: chap. 55

ታስተውል ዘንድ እመኘልሃለው።"[63] አይሁድ ከጌታ መምጣት በኋላ መጽሐፍትን ቆርጠው እንዳስወገዱ ግልጽ አድርጎ ያሳያል።

C. **የበርናባስ መልእክት(**70-100ዓም**)፡** ይህንን መልእክት ጥንት ላይ አንዳንድ ሲኖዶሶች ከሐዲስ ኪዳን መጽሐፍትም አንዱ አድርገው ይቀበሉት ነበር። ለዚህም ማሳያው በcodex sinaiticus የመጽሐፍ ቅዱስ እደክታብ ውስጥ መገኘቱ ነው። ከጳውሎስ ጋር ያገለግል የነበረው ራሱ በርናባስ እንደጻፈው የተነገረለት ይህ ጥንታዊና ተዓማኒነት የሚጣልበት ጽሁፍ እንዲህ ይላል፡ "ነቢይም በእስራኤላውያን በራሳቸው ላይ እንዲህ በማለት ተናገረ 'ኑ ጻድቁን እንግደለው፤ በእኛ ጭንቅና ጽኑዕ ሆኖብናልና'"[64] ይህ ቃል ያው ቀጥታ ከላይ ስላየነው መጽሐፈ ጥበብ 2፡12 እየተናገረ ነው።

D. **ቀለሜንጦስ ዘእስክርንድርያ(**150-215ዓም**)፡** በሕይወታችን ውስጥ በምን መልኩ ወይም ሥርዓት መኖር እንዳለብንና ከዚህ ጋር በተያያዘ ባስተማረበት ክፍሉ ላይ ስለ "ሳቅ" ሲናገር እንዲህ አለ፡ " 'አላዋቂ ሰው በሳቀ ጊዜ ቃሉን ከፍ ያደርጋል' **ይላል መጽሐፍ ቅዱስ** 'ብልህ ሰው ግን በጭንቅ ከንፈሩን ፈገግ ያደርጋል'"[65] እዚህ ላይ እንደምንመለከተው "መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል" በማለት ነው የጠቀሰው። የጠቀሰው መጽሐፈ ሲራክ 21፡20ን ነው። በእውነት በዚህ ምስክርነት ይህ አባት በነበረበት በዚያን ሰዓት እንኳን ይህ መጽሐፍ ከቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ አንዱ ለመሆኑ ትልቅ ማስረጃ ነው።

በዚሁ መጽሐፉ ላይ ስለ "አላስፈላጊ(የተጠላ) ንግግር" ሲናገር ይህንን ጥቅስ ጠቀሰ፡ "እያወቀ ዝም የሚል ሰው አለ፤ ንግግር በማብዛትም ራሱን የሚያስጠላ ሰው አለ"[66] ይህንንም የጠቀሰው ከሲራክ 20፡5 ላይ ነው።

---

[63] Dialogue with Trypho: chap. 71

[64] Epistle of barnabas, chap. 6, Philip schaff [ይህንን ጥንታዊ መልእክትና ሌሎችንም በስፋት ያዘጋጀው ፊሊፕ ስካፍ ፕሮቴስታንት ነው። ግን ደግሞ ጥሩ ዝግጅት የሚባል ነው። በዚህ መልእክት ላይ ከጥበብ መጽሐፍ መጥቀሱን ተያይዞ ሕዳጉ ላይ "This apocryphal book(Wisdom) is thus quoted as Scripture" በማለት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መጠቀሱን ይኸው ፕሮቴስታንት አዘጋጅ ይመሰክራል]

[65] The Instructor, bk. 2 chap. 5 on laughter

[66] Ibid, chap. 6 on filthy speaking

E. **የካርቴጁ ቆጵርያኖስ(**200-270ዓም**)፡** ይህም አባት ስለ ምጽዋት ማብራሪያ በሰጠበት የመጽሐፍ ክፍሉ ላይ እንዲህ አለ፡ **"መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳት መጽሐፍት በኩል እንዲህ ሲል ተናገረ** "'በእምነትና ምጽዋት ኃጢዓት ትነጻለች'(ጦቢት 12፡9) … በተጨማሪም እንዲህ አለ 'የምትነድድ እሳትን ውኃ ያጠፋታል። ምጽዋትም ሐጢዓትን ታስተሰርያለች'(ሲራክ 3፡28)"[67]

ይህ ታላቅ አባት እነዚህን መጽሐፍት መንፈስ ቅዱስ የሚናገርባቸው ቅዱሳት መጽሐፍት ይላቸዋል። ከዚህም ያለምንም ጥርጥር ከጥንትም ጀምሮ እነዚህ መጽሐፍት ከቅዱሳት መጽሐፍት የሚመደቡ እንደሆነ ግልጽ ያደርገዋል።

እንዲሁም ለቀሳውስት እና ዲያቆናቱ በጻፈው ደብዳቤ ላይም ከምስጋና በፊት ብዙ ሥራ እንደሚጠበቅ ሲናገር ይህን ጠቀሰ፡

"እስካሁን ከታየው ይልቅ ሌሎች ሊጠናቀቁ የሚገባቸው ነገሮች አሉና **እንዲህም ተጽፏል** 'ፍጻሜውን ሳታይ ሰውን አታመስግነው።'(ሲራክ 11፡28)"[68]

እስካሁን ያየናቸው አባቶች ከኒቂያው ጉባኤ በፊት ከነበሩት ውስጥ ሲሆን ይህም እጅግ በጥቂቱ ለማሳያ ያህል ብቻ አስቀመጥኩ። ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩ አባቶችን ሥራዎች ፊሊፕ ስካፍ የተባለ ፕሮቴስታንት በዘጠኝ ቅጽ(volume) አድርጎ ያዘጋጃቸው ሲሆን ለምሳሌ ሁለተኛው ቅጽ ላይ ብቻ ባሉ የአባቶች ሥራ ውስጥ ከመጽሐፈ ሲራክ ብቻ 63 ጊዜ ሲጠቀስ ከመጽሐፈ ጥበብ ላይ 28 ጊዜ ተጠቅሷል። በተቃራኒው ግን ለምሳሌ ከአስቴር፣ እዝራ፣ ሩት፣ 1ኛ ዜና መዋዕል ላይ አንድም ጊዜ ሲጠቅሱ አናይም። ከነህምያም አንድ ጊዜ ብቻ ጠቅሰዋል። ታድያ ግን ይህንን ስንል እነዚህ መጽሐፍቶች አልተጠቀሱምና ቅዱሳት መጽሐፍት አይደሉም ማለት አይደለም። ሆኖም ግን ፕሮቴስታንቱ የማይቀበሏቸው መጠቀሳቸውን ከዚህ አንጻር ስንመለከተው ቃለ እግዚአብሔር ተብለው ይታመንባቸው እንደነበረ ያሳያልና ነው። ታድያ ግን በኒቂያው ጉባኤ ሰዓትና ከዛ በኋላ ደግሞ እስከ 5ኛው ክ/ዘመን ድረስ የተነሱ አባቶችንም እንዲሁ እንጥቀስ ብንል እጅግ ብዙ በጠቀስን። ግን ይሄንን እንደናሙና ይዘን ወደ ቀጣዩ እንለፍ።

---

[67] Treatise VIII, on works and alms

[68] Epistle V:2, To the Presbyters and Deacons.

6. **አሁን ላይ ያሉ "የክርስትና ክፍሎች" ከሚቀበሉት አንጻር፡** እንደ ኦርቶዶክስ ያሉት.. ማለትም የሐዋርያዊት ኦሬንታልም ሆነ የምስራቆቹ እንዲሁም የካቶሊክንም ጨምሮ ከጥንት የመጡ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በፕሮቴስታንቱ ቡድኖች ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም የተባሉትን መጽሐፍት ይቀበላሉ። ይህም ክርስትና ከተመሰረተ ጀምሮ ለ1500 ዓመታት ያህል አብያተ ክርስቲያናት ሲገለገሉበት የነበረ ነው። ታድያ ግን በኋላ ላይ ማርቲን ሉተር የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ትቶ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" የሚል ትምሕርት ይዞ ሲመጣ ለዝች ለሥጋዊ አለም ተስማሚ ነበርና ሁሉም እየተነሳ እንደፈለገ መሆን ጀመረ። ከጥንት የመጣውንም የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ጣሉ። በእርግጥ ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን ባዘጋጀ ወቅት የብሉይ ኪዳኑን ክፍል ከዕብራይስጥ ሲተረጉም በአይሁዳውያን ዘንድ ከመጽሐፍ የወጡትን መጽሐፍት ምንም እንኳን እንደ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ባይቀበላቸውም ግን ደግሞ ጠቃሚ ናቸው በማለት በጀርመንኛ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ከሥር አብሮ አካቷቸዋል። በእርግጥ ከሥር ለይቶ ያስቀመጠው እነሱን ብቻ ሳይሆን ከሐዲስ ኪዳን ደግሞ እነ ዕብራውያን፣ የያዕቆብ መልእክት፣ የይሁዳን መልእክት እና የዮሐንስ ራዕይንም እንዲሁ ለይቶ ከሥር አስቀምጧል። ታድያ ግን እነዚህን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ቀስ በቀስ አሁን ላይ ያሉ ደግሞ ፕሮቴስታንቶች እንኳን መጽሐፋቸው ውስጥ ሊያካትቱት እንደውም አልፈው ሲነቅፉት መመልከት አስገራሚ ነው።

## የብሉይ ኪዳን ቀኖና ላይ የሚያነሷቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው:

**1. ዕዝራ ሱቱኤል፡** አንዳንድ ፕሮቴስታንቶች በውጭ የሚነሱ ጥያቄዎችን በማየት "2 esdras 14" እያሉ ሲጠቅሱ በአንዳንድ ሶሻል ሚዲያው ላይ ይስተዋላል። "ይህ መጽሐፍ 24ቱን የአይሁድ መጽሐፍት ይናገራል እንጂ ሌሎችን አይናገርም" ይላሉ። መጽሐፉ ምን እንደሚል ቃሉን በሚገባ የምንመለከተው ሲሆን መጽሐፉ "ማን ነው?" የሚለውን ግን አስቀድመን ልንመለከት ይገባል። ይህ የሚጠቅሱት መጽሐፍ የሚነግረን የዕዝራ መጽሐፍ እንደሆነና እግዚአብሔር ለዕዝራ ስለተናገረው ወይም ስለገለጠለት ራዕይ እንደሆነ ነው። ታድያ ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔር ትእዛዝ 24ቱ መጽሐፍት ብቻ እንዲነበቡ ነው በማለት ሲጠቅሱ እኛ የመጀመሪያው ጥያቄያችን ታድያ ይህንን መጽሐፍ ለምን እንደ እስትንፋሰ እግዚአብሔርነት አልተቀበላችሁትም የሚል ነው። ምክኒያቱም ይዘቱ የምሁራኑ ጽሑፍ ሳይሆን ከቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የሚካተት ማለትም የራሱ የዕዝራ መጽሐፍ ነውና። አይ የሐሰት ሥራ ነው ካሉ ግን "እግዚአብሔር ይህን አለ" ብሎ ከዚህ መጽሐፍ ላይ ማስረጃ ማምጣት በራሱ እግዚአብሔር ያላለውን እንዳለ አድርጎ በመናገር በወንጀል አያስጠይቅም ወይ? መሰረታችሁ ራሱ ሃሰት ነው አያስብልም ወይ? ሌላው ደግሞ ይህ ነገር በዕዝራ ከተነገረ ከዕዝራ በኋላ የተነሱትንም መጽሐፍት ሊወክል ይችላል ወይ? ለፕሮቴስታንቱ ፈጽሞ ማስረጃ የማይሆን ነው። በእርግጥ በተለይ እዚህ እኛ ሃገር በሶሻል ሚዲያው ለመጻፍ ጥረት የሚያደርጉ ልጆች ስለዚህ መጽሐፍ ምንም የሚያውቁትም ነገር ካለመኖሩ የተነሳ 4 ezra ወይም 2 ezra በማለት የኢንግሊዘኛውን ከመናገር በዘለለ በእኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን እንደ እግዚአብሔር ቃልነትም እንደሚካተት ስለማያውቁ "ዕዝራ ሱቱኤል" ብለው ሲናገሩም አይታይም። ለማንኛውም ይህንን መጽሐፍ እኛ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ የምንቀበለው ሲሆን "ዕዝራ ሱቱኤል" የሚል ስያሜ አለው። በሌሎች ዘንድም 3 Esdras ብለው የሚቀበሉት ሲኖሩ በላቲኑ ቩልጌት ደግሞ 4 Esdras በመባል ከሥር ተለይቶ የሚቀመጥ ነው።[69] እነሱ ጥያቄ አድርገው የሚያቀርቡትም በዕዝራ ሱቱኤል 13ኛው ምዕራፍ ላይ ያለ ነው። ቃሉ ላይ በእርግጥ አንዳንድ የሚለይ ዘርዕ ቢኖርም እስቲ እነሱ የሚጠቅሱትን የኢንግሊዘኛውን ትርጓሜ በመጥቀስ ቃሉን ለማየት እንሞክራለን።

[69] 2 Esdras book preface(New Revised Standard Version (NRSV))

መጽሐፉ አስቀድሞ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ለዕዝራ አምስት ሰዎችን ይዞ ከሕዝቡ ተለይቶ እንዲወጣና እግዚአብሔርም የእውቀትን ብርሃን በውስጡ እንደሚያኖርና እውቀትንም ገልጦላቸው መጽሐፍትን እንደሚጽፉ ይናገራል። በዚህ አርባ ቀን ውስጥ በእግዚአብሔር አነሳሽነት(Inspiration) የተጻፉ መጽሐፍት እነማን እንደሆኑ በግልጽ ባያስቀምጥም ግን ደግሞ ቃሉ በቀጥታ እንዲህ ይላል፡ "So during the forty days, ninety-four books were written. And when the forty days were ended, the Most High spoke to me, saying, "Make public the twenty-four books that you wrote first, and let the worthy and the unworthy read them; but keep the seventy that were written last, in order to give them to the wise among your people. For in them is the spring of understanding, the fountain of wisdom, and the river of knowledge"(2 Esdras 14:44-47(NRSV))

እንደምንመለከተው በእነዚህ በአርባ ቀናት ውስጥ የተጻፉት 94 መጽሐፍት ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ የተጻፉት ግን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው። ስለዚህ 94 ሙሉ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተጻፉ መጽሐፍትን ያስቀምጥና ከእነዚህም ውስጥ 24ቱን ከ70ው ሲለይ በእስትንፋሰ እግዚአብሔርነት አልነበረም። ይልቁንም እንዲህ አለው፡ "መጀመሪያ የጻፋችሁትን ሃያ አራት መጽሐፍት የሚገባውም የማይገባውም ያነበው ዘንድ ግልጥ አድርገው ፤ በኋላ የተጻፉትን ሰባውን ግን ለጠቢባን ሕዝቦች ትሰጣቸው ዘንድ ጠብቅ ፤ በእነዚህ ውስጥ **የማስተዋል መብራት ፣ የጥበብ ምንጭ ፣ የዕውቀትም ፈሳሽ** አለና።" ሰባውን መጽሐፍት የለየው እስትንፋሰ እግዚአብሔር አይደሉም በማለት ሳይሆን ለጠቢባን እንዲሰጡ ነው። በእርግጥ እነዚህ ሰባ መጽሐፍት አሉ ወይስ የሉም ራሱን የቻለ ሌላ ጥያቄ ነው። እኛ ግን ይህንን ያነሳንበት ዋናው ምክኒያት ከላይ "ቀኖና" ምን እንደሆነ ለማየት እንደሞከርነው ግዴታ የእግዚአብሔርን ቃል የመለየት ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ ተመልክተን ነበርና እርሱን የሚያጠናክር ማስረጃ ነውና ነው ይሄም።

**2. የ400 ዓመት የዝምታ ዘመን፡** በፕሮቴስታንቱ ዘንድ እንዲህ የሚል እምነት አለ.. "መጥምቁ ዮሐንስ እስኪመጣ ድረስ ከሚልኪያስ እስከ ዮሐንስ ድረስ ነቢይ አልተነሳምና እግዚአብሔር ሕዝቡን አልተናገራቸውም፤ ዝም ብሎ ነበር። ይህም በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን መካከል ያለ የ400 ዓመታት የዝምታው ዘመን ነው።"

ይህ ሃሳብ ተራ የሰዎች ፈጠራ ስለሆነ የሚወድቅባቸውን ጥቂት ነገሮች እናንሳ፡
- ይህ ሃሳብ የመጀምሪያው አስቂኝ ነገሩ ትንቢተ ሚልኪያስ በክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጨረሻ ስለተቀመጠ ብቻ መጨረሻ ላይ የተጻፈ ነው የመሰላቸው። በዚህም ምክኒያት ከሚልኪያስ እስከ ዮሐንስ የዝምታ ዘመን ነው ሲሉ እንደመስማት የሚያስቅ ነገር የለም። ሌላው ቢቀር መጽሐፈ ዜና መዋዕል ከእርሱ በኋላ ነው የተጻፈው። ለዚህም ደግሞ እንደው የራሳቸውን ድሕረ ገጽ እንዲያነቡ እስቲ እንጠቁማቸው (https://bibleproject.com/blog/sense-ending-real-last-book-old-testament/)

- ሌላው ደግሞ እንዲህ ያለ ሃሳብ(የ400 ዓመት ዝምታ) አንድም ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሌለ ነው። በተለይ ደግሞ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" እያሉ ለሚያውጁ ፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለን ነገር መናገር ነገሩን ተረት ዘፕሮቴስታንት ውስጥ እንዲመደብ ያደርገዋል።

- ይህ ሙግት ውድቅ ከሚሆንባቸው ምክኒያቶች ሌላው፡ እነዚህ ፕሮቴስታንቶች ከማይቀበሏቸው መጽሐፍት ውስጥ እነሱ "የዝምታ ዘመን" ካሉት በፊት የተጻፉ አሉ። ለምሳሌ እንደ እነ ባሮክ እና ተረፈ ኤርሚያስን መጥቀስ ይቻላል።

- ሌላው ደግሞ እዚህ ጋር ጆሴፈስን ይጠቅሳሉ፡ ጆሴፈስ በagainst apion 1:8 ላይ "ከሙሴ ሞት እስከ ንጉስ አርታዘርክሰስ( artaxerxes) ድረስ ነቢያት ሁሉ በ13 መጽሐፍት በእነርሱ ሰዓት ስለነበረው ታሪክ ጽፈው አልፈዋል።" በማለት አስቀምጧል። ታድያ ግን የፕሮቴስታንቱ ዓለም ምን ይላል ይህ ንጉስ የተባለው ሰው ዘመኑ 5ኛው ክ/ዘመን አጋማሽ ቅ/ል/ክርስቶስ በመሆኑ ከትንቢተ ሚልኪያስ በኋላ እስከ ዮሐንስ ድረስ ምንም ነቢይ አልተነሳም ይላሉ። እንደው እስቲ እውን እነሱ እንደሚያስቡት እንኳን ቢሆንና ነቢይም አይነሳ ግን ደግሞ አንድ መጽሐፍ የሚጻፈው ግዴታ በነቢይ ነው ያለው ማን ነው..?? ለምሳሌ መጽሐፈ አስቴር ወይም ደግሞ የሰለሞን መጽሐፍትም ይሁኑ ሌሎችም ተመሳሳዮች በነቢያት ነው የተጻፉት ወይ..?? ምንም እንኳን ብዙዎች ትንቢታዊ ንግግርን ቢናገሩም በማህበረሰቡ ውስጥ ግን ነቢያት አልነበሩም። ኧረ እንደውም ጭራሽ ማን እንደጻፋቸው እንኳን የማናውቃቸው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አሉ። እንዲህም ሆኖ ግን እስትንፋሰ አምላክ ብለው ተቀብለዋቸዋል። ስለዚህም እንደው ነቢይ ካልተነሳ መጽሐፍም የለም የሚለው ሙግት በራሱ ማስረጃ አጥተው ከምንም ይሻላል አይነት ጨዋታ እየተጫወቱ እንደሆነ አመላካች ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ እውነት ግንስ ጆሴፈስ ምንድን ነው ያለው የሚለውን ስንመለከት ጆሴፈስ የተናገረው ከዚያ ንጉስ በኋላ ከነቢያቱ ጋር በተያያዘ መሃል ላይ ክፍተት ሳይፈጠር በትክክል ቅደም ተከተሉን

ወይም የነቢያት መተካካቱን(succession of prophets) የጠበቀ አልነበረም ነው ያለው እንጂ ነቢያት አልተነሱም አላለም። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ በነቢያት መካከል አልፎ አልፎ የጊዜ ክፍተት ከበፊትም ይፈጠር ነበር። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ በሰባ አረተኛው መዝሙር ላይ እንዲህ ይላል "ምልክታችንን አናይም ከእንግዲህ ወዲህም ነቢይ የለም.." በማለት ይናገራል። ይህ የመዝሙር ክፍል በተጻፈበት ወቅት በሕዝቡ መካከል ከእግዚአብሔር ዘንድ ይናገር የነበረ ነቢይ አልነበረም ማለት ነው። ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል.. በ1 ሳሙ 3፡1 ላይ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን፡ "..በዚያ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ፤ ራእይም አይገለጥም ነበር።" ከዚህ የምንረዳው መሃል መሃል ላይ አልፎ አልፎ ክፍተት ሊፈጠር ይችላል የሚለውን ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ጆሴፈስ አሁንም ቢሆን ይህ የነቢያት ቅደም ተከተል መተካካቱን የጠበቀ እንዳልነበረ ሲናገር በጎን ግን ነቢያት እንደነበሩ ደግሞ እየነገረን ነው። እነዚህ ነቢያት ግን ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ አይደሉም ነው ያለውና። ይህ የጆሴፈስ ምስክርነት "ከንጉስ አርታዘርክሰስ በኋላ ነቢያት አልተነሱም" የሚለውን የፕሮቴስታንቶችን ሃሳብ ከመገፍተሩ በዘለለ ሌሎች መጽሐፍትም እንደተጻፉ ተናግሯል። ግን ደግሞ ከዛ ንጉስ ዘመን በኋላ የተጻፉት መጽሐፍት ከዛ በፊት የተጻፉትን ያህል ሥልጣን እንደሌላቸው ያምናል። ይህም ነገር ግን ትልቅ ድክመት አለበትና የራሳቸው የአይሁድ ራቢ(መምህር) የሆነው ኮኸን ሻዬ እንዲህ ብሎ ያርመዋል፡ "በሌላ አስፈላጊ ነገር ላይም ጆሴፈስ ስለ ቀኖና የሰጠው መግለጫ የተሳሳተ ነው .. በመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ውስጥ የሚካተቱት መጽሐፍት ሁሉ ከዘመነ አርታዘርክሰስ በፊት እንደተጻፉ ገልጿል .. ግን ደግሞ በእርግጥም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ መጽሐፍት ከዛ ጊዜ ብዙ ዓመታት በኋላ የተጻፉ አሉ።"[70] በማለት ይናገራል።

- ሌላው ደግሞ ፕሮቴስታንቱ "የዝምታ ዘመን ነው ለሰዎች እግዚአብሔር አልተናገረም ፤ መንፈስ ቅዱስ ከእስራኤል ርቆ ነበር" በማለት ያለ ማስረጃ እንዲሁ የአይሁድን ተረት[71] ይዘው ቢናገሩም መጽሐፍ ቅዱስ ግን በግልጽ ይህንን ተረት ሲገልጠው እንመልከት፡ በሉቃስ 1:65-66 ላይ እንዲህ ይላል፡ "አባቱ ዘካርያስም **መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ** እንዲህም አለ: የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፥ ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና።" ይህ እንግዲህ ከዮሐንስ አገልግሎት በፊት ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ከሕዝቡ እንዳልራቀና ትንቢትም ይነገር እንደነበረ ያሳያል። ተጨማሪ ከዚህ ከሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ላይ የምናገኛቸው ሁለት ሰዎች አሉ። እነዚህም የመጀምሪያው አረጋዊው

[70] From The Maccabees to The Mishnah
[71] The Babylonian Talmud: TRACT SANHEDRIN, chap. 1

ስምኦን ሲሆን ይህም ጌታ በተወለደበት ወቅት የነበረና የጌታን የመወለድ ቃል ከእግዚአብሔር በመንፈስ የተቀበለና ሳያየውም እንዳይሞት የተነገረለት የጌታን መወለድ ይጠባበቅ የነበረና በተወለደም ጊዜ ጌታን ያቀፈ ሰው ነው። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፡

“እነሆም፥ በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበረ፥ ይህም ሰው **የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር**፤ ጻድቅና ትጉህም ነበረ፥ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ። በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ **በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ** ነበር።”(ሉቃ 2፡25-26)

እግዚአብሔር አምላክ ይህንን ሰው ትንቢትም ሲያናግረው እንመለከታለን፤ ትንቢቱም እንዲህ የሚል ነው፡

“ስምዖንም ባረካቸው እናቱን ማርያምንም እነሆ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ፤ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፤ **በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት**።”(2፡ 35)

ሁለተኛዋ በዚሁ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሰችው ደግሞ ቀጥታ ነቢይት ተብላ ነው፡ “ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት **ነቢይት** ነበረች”(2፡ 36) ይህችም ነቢይት በሚያስገርም ሁኔታ የጌታን መምጣት እንደ ፈሪሳውያን ሳይሆን ቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር እንደተነጋገሩት ነቢያት ትጠባበቀው ነበርና ጌታ በተገኘበት ቤተ መቅደስ ቀርባ እግዚአብሔርን እንዳመሰገነችና የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር እንደ ነበር ተገልጿል።(2፡ 38)

በእነዚህ ሰዎችም እንደምንመለከተው የክርስቲያኖች አምላክ በየትኛውም ዘመን ላይ ከሕዝቡ ጋር ይነጋገር እንደነበረ ነው።

**3. የጃሚኒያ ጉባኤ(council of jamnia):** በ97ዓም አካባቢ ያምኔ(ጃምኔ) በተባለ አካባቢ አይሁዳውያን ጉባኤ አድርገው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ካኖናይዝ አድርገዋል ወይም ደግሞ አንዳንዶች ጋር የተሻለ የተናገሩ የሚመስላቸው ደግሞ ከዛ በፊትም ይጠቀሙበት የነበረውን 24ቱን መጽሐፍት እንደሆነ አጽድቀዋል የሚል ታሪክ አለ። ይህንን በመያዝ አንዳንድ ፕሮቴስታንቶች ብሉይ ኪዳን የአይሁድ ነውና እነሱ መጽሐፉቸውን ያውቃሉ እና እነሱ ካኖናይዝ ያደረጉት ነው ትክክል፤ ካኖናይዝ ሲያደርጉም አሁን ላይ ማሶሬቲክ ቴክስት ላይ እንዳለው ነውና 39ኙን የአይሁድ መጽሐፍት

ብቻ ነው የምንቀበለው ይላሉ።በመጀመሪያ ደረጃ ይሄ በጃምኒያ ጉባኤ አይሁዳውያን የብሉይ መጽሐፍትን ካኖናይዝ አድርገዋል የሚል ታሪክ ከተረትም የዘለለ አይደለም። ምናልባትም ደግሞ ፕሮቴስታንቱ እንዲህ እንዲሆን ስለሚመኙ ብቻ የሚሉት ነገር እንጂ ተረቱ እንደ ታሪክ መሰማት የጀመረው እንኳን አሁን በቅ ርብ ከ19ኛው ክ/ዘመን በኋላ ነው። በኋላ ግን ይኸው ተረት በሌሎች የፕሮቴስታንት ሊቃውንቶችም ትችት ይደርስበት ጀመረ። አሁን ላይ ያን ያህልም ተቀባይነት የለውም። ብሩስ(F.F. Bruce) የተባለ የፕሮቴስታንት ጸሐፊ እንደተናገረው "የብሉይ ኪዳንን ቀኖና የሚወስን ጉባኤ በጃምኒያ አለ ብሎ መናገር ሞኝነት ነው።"[72] ምንም ጥንታዊ ታሪክ የሌለው ተረት ይዞ መሞገት የተረት አባት ያስብላል። እንደ አዲስ ካኖናይዝ አለማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ጭራሽ ስለ 24ቱ መጽሐፍትም አልተነሳም። አንዳንዶች እንደሚሉት በመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ ትክክለኛነት ላይ ነው የተነጋገሩት የሚባልም ነገር አለ። ግን ደግሞ ሲጀመር የጃምኒያ ጉባኤ የሚባል ነገር ራሱ ይኑር አይኑር ማስረጃ የለም። እንዲሁ የፈጠራ ወሬ ይመስላል። ካልሆነማ ጥንታዊ ማስረጃም በቀረበበት ነበር።

ግን ደግሞ ቢሆንና እውን ጉባኤ አድርገው ቢሆንስ ኖሮ፤ እውን እሱ ራሱ ማስረጃ መሆን ይችላል..?? ክርስቶስ መጥቶ አንቀበልህም ብለው የሰቀሉት የእርሱ ተከታዮችንም ሲያሳድዱ የነበሩት እነሱ እኮ መናፍቃን ናቸው። ታድያ ምን ቢሉስ እንዴት እንደ ማስረጃ ይጠቀሳሉ..?? ወይስ ጌታ የሐዲስ ኪዳንን ቤተክርስቲያን ከመሰረተ በኋላም በአይሁድ በኩል ነበር የሚሰራው..?? መቼስ ይሄንን ደፍሮ የሚናገር የለም ምክኒያቱም የጌታ ጠላት ሆናለች አይሁድ። በዚህም ምክኒያት የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበረችው አይሁድ በእነርሱ ዘንድ ጠፍታ ስሙን ብቻ ይዘዋል። ለዚህም ደግሞ ጌታ "የሰይጣን ማሕበር" ይላቸዋል። እንደውም ፕሮቴስታንቶች ከእነዚህ ጋር በመተባበራቸው እነሱን ራሱ የክርስቶስ እና የአካሉ ማለትም የቤተ ክርስቲያን ጠላት "የሰይጣን ማሕበር" ናቸው ያሰኝባቸዋል።

**4. Flavius Josephus(ጆሴፈስ)፡** ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ይህ በመጀመሪያው ክ/ዘመን አካባቢ የነበረ አይሁዳዊ የታሪክ ምሁር ነው። ይህ ሰው በ90ዎቹ ዓ.ም አካባቢ የጻፈውን በመጥቀስ የአይሁድን ትክክለኛ መጽሐፍት አስቀምጦ አልፏል ይህም እኛ ምንቀበላቸውን 39ኙን ነው የሚሉ አሉ። ምንም እንኳን የጆሴፈስ ሥራ ጥንታዊ ከመሆኑ አንጻር አንዳንድ ማስረጃዎችን ከእርሱ መፈለጉ ባይከፋም ክርስቶስ ከመጣ በኋላ የመጣ ሰው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ግን ትልቅ ጥንቃቄ የሚፈልግ

[72] F.F. Bruce: The canon of scripture. Pg 34

ነው። ምክኒያቱም ከላይ እንዳልነው አይሁድ የክርስቶስ ጠላት ሆናለች ስለዚህም እስራኤል መባሏ በሃገር ስም ካልሆነ ዋናውን ትርጓሜ የያዘውን ስም አጥታዋለች። አሁን ላይ "እስራኤል" እኛ ክርስቲያኖች ነን። እስራኤል ማለት "ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ያሸነፈ" ሕዝበ እግዚአብሔር ማለት ነውና። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ደግሞ በጌታ ኢየሱስ ያመንን በደሙም የቀረብን(ኤፌ 2፡11-13) እንጂ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስን ጠላት ያደረጉት አይሁዳውያን አይደሉም። ይህ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍም በቤተ ክርስቲያን በኩል እንጂ የሚጠበቀው በአይሁድ በኩል አይደለም። ጆሴፈስ(Josephus) ደግሞ አይሁዳዊ ነውና በእዚህ ርዕስ ላይ የጻፈውን ጽሑፍ እንደ ትልቅ ነገር የምናየውም አይደለም።

እውን ግን ጆሴፈስ ፍላቪያኑስ ስለ አይሁድ መጽሐፍት ሲናገር አሁን ፕሮቴስታንቶች ወይም አይሁዳውያን እጅ ላይ ባለው መልኩ ነው..?? ጆሴፈስ ከእነርሱ ጋር እንኳን የሚጋጭ ገና ከጅምሩ ማስረጃ እንኳን የማይሆናቸው ሰው ነው። ምክኒያቱም ጆሴፈስ የአይሁድ መጽሐፍት 24 ናቸው አላለም። ይልቁንም 22 ናቸው ይላል።[73] ይህንን ደግሞ ይዞ ይኸው ኮኸን ሻዬ የተባለው የታሪክ ምሁር እንዲሁም በእብራይስጥ ጽሑፍና ፊሎሶፊ phd ያለው በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የሆነ የአይሁድ መምህር(Rabbi) እንዲህ አለ፡ "ጆሴፈስ ብዙም እውቀት አልነበረውም(በመጽሐፍት ብዛት ላይ) ወይም ደግሞ ሆን ብሎ እያሳተ ነው"(Josephus is either poorly informed or deliberately misleading)[74] ታድያ የራሳቸው የአይሁድ ምሁር እንዲህ ከተናገረ እንዴት ማስረጃስ ሆኖ ይቀርባል? 22 መጽሐፍት ማለቱ እንዳለ ሆኖ የጆሴፈስን ንግግር ይዘን ምንም ስለ መጽሐፍት ልንናገር የማንችልበት ሌላው ትልቁ ምክኒያት ደግሞ ጆሴፈስ እነዚህ 22 መጽሐፍት እነማን እንደሆኑ እንኳን አለመናገሩ ነው። ግን ደግሞ የመጽሐፉን አከፋፈል አስቀምጧል። ይህም ደግሞ ሌላ ትልቅ ውዥንብር ውስጥ የሚከት ነው። ይህንን ደግሞ ለማስተዋል አስቀድመን የአሁኖቹን አይሁድ መጽሐፍ አከፋፈል እንመልከት፡

የማሶሬቲክ ቴክስት መጽሐፍ (ታናክ) ሦሥት ክፍሎች አሉት ብለናል።

1. **Torah(ቶራህ)**፡- ይህ ክፍል የሚይዘው **አምስቱን(5)** የሕግ መጽሐፍት ነው።

---

[73] The Complete Works of Josephus: against apion 1:8

[74] Cohen, Shaye: From The Maccabees to The Mishnah 2nd ed: pg 181

2. **Neviim(ኔቪኢም)**፡- ይህ ደግሞ በነቢያት የተጻፉ የትንቢት መጽሐፍትን ሲያመለክት አጠቃላይ የትንቢት መጽሐፍት **ስምንት(8)** ናቸው። አስራ ሁለቱን ደቂቀ ነቢያት(minor prophets) እንደ አንድ ነው የሚቆጥሩት። ሌሎች የቀሩት ሰባቱ ደግሞ፡ ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል(1ኛ እና 2ኛ)፣ ነገስት(1ኛ እና 2ኛ)፣ ኢሳያስ፣ ኤርሚያስ እና ሕዝቅኤል ናቸው።[75]

3. **Ketuvim(ኬቱቪም)**፡- ይህ በአጠቃላይ "ጽሑፎች" ተብለው የሚያዙ ሲሆኑ በቁጥር **አስራ አንድ(11)** ናቸው። ያው እንግዲህ ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ የቀሩት መሆናቸው ነው። ስለዚህም የመጽሐፍቱ ቁጥር፡ 5+8+11 = 24 ሆነ። ይህንን ያህል ስለ ታናክ(Tanakh) መጽሐፍ አከፋፈል ካየን እስቲ የጆሴፈስን ደግሞ እንመልከት። ጆሴፈስ መጀመሪያ "አምስቱ የሙሴ መጽሐፍት" በማለት ይጀምራል። ይሄ ሁሉንም ያስማማል። ከዛም በመቀጠል ነቢያት የጻፏቸው ብሎ አስራ ሦስት(13) መጽሐፍት ይላል። ተመልከት የትንቢት መጽሐፍት 13 ናቸው ብሏል።[76] ግን ደግሞ ከላይ እንዳየነው በታናኩ ላይ 8 የትንቢት መጽሐፍት ነው ያሉት። ጆሴፈስ ግን 13 እንዳሉ ነው የሚያምነው፤ ይህም በ5 ብልጫ ያሳያል። ምናልባት እንደ አይሁዳውያን 12ቱን ደቂቀ ነቢያት እንደ አንድ ቆጥሮ ከሆነ ሌሎች 12 የትንቢት መጽሐፍት ይኖሩታል.. ይህ ደግሞ አይሁድ ከሚቀበሏቸው በአምስት ይበልጣል.. የተቀበላቸው እነማን ይሆኑ..?? አልገለጸውም። ምናልባት ደግሞ 12ቱን ደቂቀ ነቢያት ከአይሁድ በተለየ መልኩ አንድ አንድ አድርጎ ከቆጠራቸው ከእነሱ ውጪ አንድ ብቻ የትንቢት መጽሐፍ ሊቀበል ነው። የቷ ትሆን..?? አናውቅም። እውን እንዲህ የተወዛገበ ነገር በሞላበት ሁኔታ እንደ ማስረጃ እንኳን ይቀርባል..?? ታድያ ጆሴፈስ 22 መጽሐፍ ብሎ ሲናገር ይህንን ይዘው በመጽሐፉ ሕዳግ(footnote) ላይ አሁን ፕሮቴስታንቱ ከተቀበለው መጽሐፍ ውስጥ ለምሳሌ መኃልየ መኃልይን እና መጽሐፈ ዕዝራን እንደማይቀበልና በተቃራኒው ደግሞ ጭራሽ እነሱ የማይቀበሉትን ግን ደግሞ እኛ የምንቀበለውን ዕዝራ ካልእ(First Esdras) እንደሚቀባል ይናገራሉ። ታድያ ዕዝራ ካልእ በአይሁዶች ዘንድ ተቀባይነት ከነበረው ምነው ዛሬ ላይ የተነሳው የፕሮቴስታንቱ(የተቃውሞው) ዓለም ይህንን መቀበል ተሳነው..?? ከላይ ጀምረን እንዳየነው እነሱ ለያዙት መጽሐፍ ጆሴፈስ ማስረጃ እንኳን አይሆንም። ሌላው ደግሞ

---

[75] ፕሮቴስታንቶች የአይሁድን አከፋፈል አይቀበሉም። ምንም እንኳን እነሱም ለሦስት እንደሚከፍሉት ቢያስቡም መጽሐፍቱ ግን እኛ በምናስቀምጥባቸው ክፍሎች ላይ ነው ያስቀመጧቸው። ለምሳሌ እዚህ ላይ ያየናቸውን የመጀመሪያዎቹን አራቱንም ከትንቢት አይመድቧቸውም።

[76] Against apion 1:8

ጆሴፈስ 22 መጽሐፍት እንዳሉ ሲናገር ስለ ቀኖና እያወራ አልነበረም። ገና ከጅምሩ ከላይ እንዳየነው አይሁድ የመጽሐፍት ቀኖናም የላቸውም። ይልቁንም ጆሴፈስ ይህንን ሲናገር "በግሪካውያን ዘንድ እንዳለው ብዙ መጽሐፍት የሉንም" በማለት ነበርና በሰዓቱ እርሱ ካለው 22 መጽሐፍት ውጪም ሌሎች የግሪክ መጽሐፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ተብለው ለመቀመጣቸው ጥሩ ማሳያ ነው።

**5. መጽሐፈ ኩፋሌ እና ሄኖክ ከኢትዮጵያ ውጪ አለመገኘታቸው፡** ሌላው የሚነሳው ጥያቄ መጽሐፈ ኩፋሌና መጽሐፈ ሄኖክ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ እንጂ ሌላ ቦታ የሉም የሚል ነው። ይህንን ጥያቄ በአጭሩ ለመመለስ ያህል እነዚህ መጽሐፍት ብዙም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር ሳይደርሱ መጥፋታቸው ነው። ታድያ ግን ሌላው ዓለም ላይ ሲጠፉ እኛ ሃገር ላይ ተጠብቀው ቆይተዋልና እንቀበላቸዋለን። ምናልባት ግን ይህንን ስንል ገና ከጅምሩ መኖራቸው እንኳን ሳይታወቅ እንዴት ስለመጥፋት ይወራል መባሉም አይቀርምና ጥቂት ማስረጃ ለመስጠት ያህል እነዚህን መጽሐፍት የኩምራን አይሁድ ማሕበረሰብ ከሌሎች ቅዱሳት መጽሐፍት ጋር ይጠቀሙባቸው እንደነበረ ከላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ላይ ካቀረብናቸው ማስረጃዎች ውስጥ የመጀመሪያው ላይ ተመልክተናል። በተለይ መጽሐፈ ኩፋሌ ወደ 15 የሚሆኑ ጥቅሎች በመገኘታቸውና ይህም ደግሞ ከሌሎች ቅድሳት መጽሐፍት ጋር እንኳን ሲነጻጸር ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹን ይበልጣልና እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ተቀብለውት እንደነበረ ማሳያ ይሆናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ስለ መጽሐፈ ኩፋሌ ብሩስ(FF Bruce) የተባለው የፕሮቴስታንቱ ጸሐፊም እንደመሰከረው በዛው በኩምራን የተገኘው "The Zadokite Work" የተሰኘው የአይሁድ ሰነድ መጽሐፈ ኩፋሌን ሥልጣን ሰጥቶ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገርለትና ይህ የቁምራኑ ጥናት በተደረገበት ወቅት የነበረ Yigael Yadin የተባለ በእነዚሁ የቁምራን ግኝቶች ላይ እጅጉን የሰራ እስራኤላዊ አርኪዮሎጂስት መጽሐፈ ኩፋሌን እንደ ቀኖና መጽሐፍ ይቀበሉት እንደነበር ይሞግታል ብሏል።[77]

መጽሐፈ ሄኖክን በተመለከተም እንዲሁ በዚሁ ግኝት ላይ በስፋትና በተለያዩ ቋንቋዎች ከተገኙ ቅዱሳት መጽሐፍት አንዱ ነውና ከክርስቶስ መምጣት በፊትም አይሁዳውያን ይጠቀሙበት እንደነበረ ግልጽ ነው። ክርስቶስ ሲመጣም ሐዋርያትም ይጠቀሙበት ነበር። ለዚህም ማሳያው ይሁዳ በመልእክቱ እንዲህ ብሎ መጥቀሱ ነው፡ "**ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ** እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥

[77] Ibid, pg. 40

በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ **ትንቢት ተናገረ።**"(ይሁዳ 15) ይህ ሐዋርያ ሄኖክ የተናገረውን እንደ ትንቢት ከተቀበለ ያው ሐዋርያት ከሚቀበሏቸው ቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ አንዱ ነበር ማለት ነው። በበርናባስ መልእክት ውስጥም "ሄኖክ እንደተናገረው" ተብሎ ተጠቅሷል[78] በሌሎችም ጥንታውያን አባቶች በተለይ ሰማዕቱ ዮስቲን ከአይሁዳዊው ትራፎን ጋር ባደረገው ውይይት ላይ መጽሐፉ ላይ ያሉ ነገሮች ሲነሱ ማየት ይቻላል።[79] ከዚህ ጋር በተያያዘ ግን በኢትዮጵያም በሰሜኑ አካባቢ የሚኖሩ የአይሁድ ማሕበረሰብ እነዚህን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ይጠቀሙባቸዋል።

**6. ከቤተ ክርስቲያን አባቶች(አትናቴዎስ፣ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም እና ጀሮም):** ፕሮቴስታንቶች አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባቶችን በመጥቀስ እኒህ አባቶች ደግሞ 39ኙን ፕሮቴስታንቶች የሚቀበሏቸውን መጽሐፍት ብቻ እንደ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚቀበሉ በመናገር እንደ ማስረጃነት ለማቅረብ ይሞክራሉ።

ፕሮቴስታንቶች ማስረጃ ቢሆኑን ብለው የሚጠቅሷቸውን አባቶች ለማየት እንሞክራለን። እስቲ ከቅዱስ አትናቴዎስ እንጀምር:

**ቅዱስ አትናቴዎስ:**

አትናቴዎስ በ39ነኛው Festal Letter(የፋሲካው ደብዳቤ) ላያ አስቀድሞ ስለ የመናፍቃን መጽሐፍ ያስረዳል። እነዚህም መጽሐፍት በቅዱሳን ስም እየተደረጉ እንደተጻፉና ምንጫቸው ግን መናፍቃኑ በመሆናቸው ልንይዛቸው እንደማይገባ በአጭሩ አርቀን እንድንጥላቸው ያስረዳል። የሃሰት መጽሐፍትን ከእውነተኞቹ ከለየ በኋላ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን የቁጥር ብዛት በእብራይስጥ አልፋቤት 22 ፊደላት ልክ በማድረግ 22 ናቸው ብሎ የዘረዘራቸው አሉ: ከእነርሱ ውስጥ ደግሞ ለምሳሌ አንዱ **መጽሐፈ ባሮክ** ነው። ፕሮቴስታንቶች ይህንን አይቀበሉም ግን አትናቴዎስ የሚቀበለውን እንደሚቀበሉ በማስመሰል ለመጥቀስ ይሞክራሉ። ይህ ብቻም አይደለም ተጨማሪ መጽሐፍ እንጥቀስ **ተረፈ ኤርሚያስ**(letter of jeremiah) በአትናቴዎስ ቀኖና ውስጥ የተካተተ ነው። ታድያ ግን ፕሮቴስታንቱ ይህንንም መጽሐፍ

[78] Epistle of barnabas: 4

[79] Justin Martyr: dialogue with trypho, chap. 79

አይቀበልም። ሌላ ሁለት ተጨማሪ መጽሐፍትም ልንጠቅስ እንችላለን፤ እነዚህም **ዕዝራ ካልእ** እና **ዕዝራ ሱቱኤል** ናቸው። እነዚህን ሁለት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ይህ ሊቅ ሲያስቀምጥ "First and Second Esdras(1ኛ እና 2ኛ እዝራ)" በማለት ሲሆን እነዚህ መጽሐፍት ከእኛ "ዕዝራ ካልእ እና ዕዝራ ሱቱኤል" ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ከእነዚህ ሁለት መጽሐፍት ውስጥ የጆርጅያ ኦርቶዶክስ ሁለቱንም ይቀበላሉ፣ የምስራቅ ኦርቶዶክሶች ዕዝራ ካልእን ይቀበላሉ።[80] ካቶሊክ ወንድሞቻችን እነዚህን መጽሐፍት አይቀበሉም። ይህ አለመቀበላቸው ደግሞ ከፕሮቴስታንቱ ጋር ተደመረና እነዚህን በአትናቴዎስ የተጠቀሱ ሁለት መጽሐፍት "ዕዝራ እና ነህምያ" እንደሆኑ መናገር በብዙዎች ዘንድ የተለመደ ሆነ የሚል ግምት አለኝ። ለማንኛውም ግን ልንረዳው የሚገባው ነገር "ዕዝራ እና ነህምያ" ለማለቱ ማስረጃ አያቀርቡም። እኛ ግን የተወሰነ ለመመልከት እንሞክር፡ አርጌንስ(origen) 22ቱ የአይሁዳውያን መጽሐፍት ብሎ ሲዘረዝር እንዲሁ "Esdras, first and second(ዕዝራ 1ኛ እና 2ኛ)" በማለት ካስቀመጠ በኋላ ዕዝራን ደግሞ እንዲሁ ለብቻው ለይቶ ይጠራዋል።[81] ይህ ማለት አርጌንስ አስቀድሞ የጠራቸው ሁለት መጽሐፍት ውስጥ ቢያንስ ዕዝራን እንደማያካትት ያስረዳል፤ ምክኒያቱም ዕዝራን ለብቻው ለይቶ ሁለተኛ ስለጠራው። እንዲህ እንዳለ ሆኖ ግን አትናቴዎስ "ዕዝራ ካልእን እና ሱቱኤልን" እየጠራ እንደሆነ ሌላው ማሳያችን በሥራዎቹ ላይ እነዚህ መጽሐፍት መጠቀሳቸው ነው። ለምሳሌ አትናቴዎስ ከዕዝራ ሱቱኤል እንዲህ ሲል ይጠቅሳል፡

"ነቢዩም ከጥንት ጀምሮ እጅጉን አስምቶና በግልጽ የአብን ከእርሱ(ከወልድ) ጋር መኖር እንዲህ በማለት አስረዳ፡ 'ልጄን ክርስቶስን እልካለሁ'"[82] (ሱቱኤል 5፡28-29)[83]

በዚህ መልኩ ከሱቱኤል ሲጠቅስ ከዕዝራ ካልእም እንዲሁ በፊሊፕ ስካፍ የindex ቆጠራ መሰረት ወደ 4 ጊዜ ጠቅሶታል። ይህም ፊሊፕ ስካፍ ባዘጋጀው በተመረጡ የአትናቴዎስ ሥራዎች ውስጥ ብቻ ነው። ታድያ ግን ቅዱሱ አባታችን እነዚህን ሁለት መጽሐፍት በሥራዎቹ ውስጥ በቀጥታ ሲጠቅሳቸው በተቃራኒው ደግሞ በቀኖና ውስጥ ካላካተታቸው ከዕዝራና ነህምያ መጽሐፍት ቀጥታ ከእነሱ እንደጠቀሰ የሚያሳይ አንድም ማስረጃ የለም። እርግጥ ነው በሥራዎቹ ላይ እነሱን አልጠቀሰም የሚለው ሃሳብ

---

[80] The orthodox study bible

[81] Eusabius, ecclesiastical history: 6:25, Philip schaff, NPNF2,2

[82] Discourse against the arians, 4:33

[83] New Revised Standard Version(NRSV) በተሰኘው የኢንግሊዘኛ ትርጓሜ እንዲሁም በKJV ላይም 2 esdras 7:28-29 ላይ ይገኛል።

እነዚህ መጽሐፍት ቀኖና ውስጥ አልተካተቱም ወደሚል ድምዳሜ አያደርስም። ሆኖም ግን በቀኖና ውስጥ የጠራቸው እነዚህ ሁለት መጽሐፍት እነማን እንደሆኑ ለመረዳት ፍንጭ ይሰጡናል። ስለዚህም ፕሮቴስታንቶች ከማይቀበሏቸው መጽሐፍት ውስጥ ባሮክ፣ ተረፈ ኤርሚያስ፣ ዕዝራ ካልእ እና ዕዝራ ሱቱኤል በአትናቴዎስ ቀኖና ውስጥ ሲካተቱ በተቃራኒው ደግሞ ፕሮቴስታንቱም ከሚቀበሏቸው መጽሐፍት ውስጥ አስቴርን፣ ዕዝራን እና ነህምያን አትናቴዎስ በቀኖናው ውስጥ አላካተታቸውም። ታድያ ግን ይህ ታላቅ አባት ቀኖና መጽሐፍት ብሎ ያስቀመጣቸው እንዴት ነው? እዚህ ቀኖና ላይ ያልተካተቱትስ እስትንፋሰ እግዚአብሔር አይደሉም? የሚለውን ነገር ለመመልከት እንሞክር፡ ማርክ ቦኖኮር(Mark Bonocore) የተባለ የካቶሊክ ጸሐፊ ከዚህ ቀኖና ጋር በተያያዘ ሲያብራራ[84] ገና ከጅምሩ አትናቴዎስ እነዚህን መጽሐፍት በቀኖና ሲያስቀምጥ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተጻፉትን መለየቱ ሳይሆን አትናቴዎስ የአሌክሳንድሪያ ፓትሪያርክ እንደመሆኑ በዛች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዛን ጊዜ በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡትን በቀኖና ማስቀመጡ እንደሆነ ይናገራል። ይህ ሃሳብ ማለት ከላይ ቀኖናን ስንመለከት ከዕዝራ ሱቱኤልም አንስተን ካብራራንበት ሃሳብ ጋር የሚመሳሰል ትክክለኛ መረዳት ነው። ይህንን ማብራሪያ ለመረዳት ግን እስቲ አንዳንድ ነገሮችን አንስተን እንመልከት፡

1. አትናቴዎስ ይህንን ቀኖና ባስቀመጠበት ክፍል ላይ አስቀድሞ ስለ **አፖክሪፋል** መጽሐፍት ሲናገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንደማይካተቱና የመናፍቃን ሥራዎች እንደሆኑ በመናገር ከእነርሱ እንድንርቅ ሲያስጠነቅቀን፤ መጽሐፈ አስቴርን፣ ዕዝራን እና ነህምያን ጨምሮ ስለእነዚህ ከቀኖና ውጭ ስላደረጋቸው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ግን ሲናገር "ሌሎችም መጽሐፍት ደግሞ አሉ" በማለት እነዚህን "እግዚአብሔርን የመምሰል ቃል ላይ መመሪያን የሚሹ ሁሉ ያነቡት ዘንድ ከአባቶች ተቀብለናቸዋል"[85] በማለት እግዚአብሔርን በመምሰል ሕይወታችን ውስጥ ወደ ጽድቅም የሚመሩ ስለሆኑ እንድናነባቸው ይነግረናል። ሃዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቅዱሳት መጽሐፍት ሲናገር በ2ጢሞ 3፡17 ላይ፡ **"የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ** ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" በማለት በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተጻፉ መጽሐፍትን ይናገራል። አትናቴዎስም የለያቸው መጽሐፍት ለእነዚሁ ጥቅምም የሚረዱ ናቸውና እነዚህን መጽሐፍት የለየው ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚነበቡት ነው ያስብላል።

[84] "Did Some Church Fathers Reject the Deuterocanonicals as Scripture" internet article by math1618
[85] Festal letter 39:7

2. ከላይ ያለውን ሃሳብ የሚያጠናክርልን ሌላው ትልቅ ማስረጃ አትናቴዎስ ምንም እንኳን የቀኖና መጽሐፍት በመላት የዘረዘራቸው መጽሐፍት ቢኖሩም በፊሊፕ ስካፍ(Philip schaff) በተዘጋጀው "የተመረጡ የአትናቴዎስ ሥራዎችና ደብዳቤዎች" በተሰኘው ጥቂት ሥራዎቹን በያዘው መጽሐፍ ላይ ብቻ ከእነዚህ የቀኖና መጽሐፍት ከተባሉት ውጪ ካሉት መጽሐፍት ውስጥ 42 ጊዜ ጠቅሷል። ምናልባት መጽሐፈ ባሮክን ጨምረን ከተመለከትናቸው ደግሞ ከ50 የማያንሱ ይሆናሉ።[86] ከጠቀሳቸውም ውስጥ ደግሞ ምሳሌ እንጥቀስ፡

- "ስለ እነዚህና የመሳሰሉት የጣኦት ፈጠራዎች ግን አስቀድሞ ከብዙ ጊዜ በፊት **መጽሐፍ ቅዱስ ያስተማረን ነው** 'የዝሙት መጀመሪያ ጣዖትን የመስራት ሃሳብ ነውና እርሱንም ማግኘት የሕይወት ጥፋት ነው ……'" (ጥበብ 14፡12-21)[87]

በዚህ ቦታ ላይ እንደምንመለከተው ታልቁ አባት አትናቴዎስ በቀኖናው ውስጥ ካላካተታቸው መጽሐፍት ውስጥ አንዱ ከሆነው መጽሐፈ ጥበብ ጠቅሶ ሲያስረዳ እንመለከተዋለን። ታድያ ግን መጥቀስ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎች ምክኒያት እንኳን እስካያገኙ ድረስ "መጽሐፍ ቅዱስ" ብሎት ነው። **ስለዚህም አትናቴዎስ መጽሐፈ ጥበብን ከቀኖና ውስጥ አስወጣው ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስወጣው ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ያደርገዋል።**

- "**መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው** '[ከእርሱ በኋላ እንደ እርሱ ያለ ልጅ ተከቷልና] አባቱ ቢሞትም እንዳልሞተ ይሆናል'"(ሲራክ 30፡4)[88]

በተመሳሳይ መልኩ አሁንም ቀኖና ውስጥ ካላካተታቸው መጽሐፍት ውስጥ አንዱን ሲራክን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚካተት እስክንድሮስ ሲናገር ያለምንም ተቃውሞ አረጋግጦ ያሳለፈበት ነው።

- "እንዲሁም ክርስቶስ እስትንፋስ ተብሏል፤ 'የእግዚአብሔር የኀይሉ እስትንፋስ ነውና"'(ጥበብ 7፡ 25)[89]

በዚህም ቦታ ላይ ዲዮናስዩስ የክርስቶስን ዘላለማዊነት ዶግማዊ ትምሕርት የመሰከረበትን ይዞ ሲናገር ከቀኖና ውጪ የሆነውን መጽሐፈ ጥበብንም በመያዝ እውነትም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ

---

[86] Philip schaff, NPNF2: vol. 4, index
[87] Against the heathen, part I:11
[88] Defence against the Arians, 66
[89] Defence of Dionysius, 15

በመመስከር ሲሆን ይህንንም አትናቴዎስ ያለምንም ተቃውሞ ይልቁንም ደግፎት ስለ ዲዮናስዩስ የተከላከለበት ጽሑፍ ነው።

- "እርሱ[ጌታችን ኢየሱስ] የእግዚአብሔር ቃል፤ ኃይልና ጥበብም ነውና፤ ስለ ጥበብም **ሰለሞን እንደመሰከረው** 'አንዲት ስትሆን ሁሉን ማድረግ ትችላለች ራሷ እየነሮች ሁሉን ታድሳለች፤ በየትውልዱም በጻድቃኑ ሰውነት ትተላለፋለች የእግዚአብሔርም ወዳጆችና ነቢያት ታደርጋቸዋለችና'"(ጥበብ 7፡27)[90]

በዚህ ቦታ ላይም ጌታችን ኢየሱስ በነገሮች የማይወሰን ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉን ቻይ እንደሆነ ሲያስረዳ "ሰለሞን እንደመሰከረው" በማለት ከመጽሐፈ ጥበብ በመጥቀስ ነው።

- "እነርሱም(ምስጢራትን ላልተጠመቁት የሚያቀቡት) **የተጻፈውን** ይመለከቱት(ይመሩበት) ዘንድ ይገባል፡ 'የመንግስትን ምስጢር ሊሰውሩት ይገባል'(ጦቢት 12፡7)፤ ጌታም 'የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፥ ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ'(ማቴ 7፡6) በማለት እንዳዘዘን።[91]

በዚህ ቦታ ላይ ደግሞ አሁንም በቀኖናው ውስጥ ያላካተተውን "መጽሐፈ ጦቢትን" እና ቀኖና ውስጥ ካካተተው ደግሞ "የማቴዎስ ወንጌልን" በአንድነት በመጥቀስ "በመጽሐፍ የተጻፈውን" ብሎ ያስረዳል።

በእውነት ከእነዚህ ጥቂት ምስክርነቱ እንኳን እንደምንመለከተው አትናቴዎስ "ቀኖና" ብሎ ያስቀመጠው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚካተቱ መጽሐፍት እንዳልሆነ ግልጽ ያደርገዋል።

**ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም** ጋርም ስንሄድ ይህ አባት 22ቱን የብሉይ መጽሐፍት ግን ደግሞ የእብራይስጡን ሳይሆን የሰብዓው ሊቃናትን ትርጓሜ እንድናነብ እና አፖክሪፋል ብሎ ከገለጻቸው የመናፍቃን መጽሐፍት እንድንጠበቅ ይመክረናል። የቶማስ ወንጌልንም ለአፖክሪፋል መጽሐፍት እንደ ምሳሌ በመጥቀስ የአትናቴዎስን የቀኖና አገላለጥ የሚመስል የመጽሐፍት ዝርዝርን "ቀኖና" የሚል ቃል ሳይጠቀም "በቤተ ክርስቲያን የሚነበቡ" በማለት ያስቀምጣል።[92] ቄርሎስ በቀኖናው ውስጥ ፕሮቴስታንቱ ከማይቀበሏቸው መጽሐፍት ውስጥ ባሮክንና ተረፈ ኤርምያስን እንዲሁም እንደ አትናቴዎስ

[90] Festal letters 10:4

[91] Defence against the Arians, 11

[92] Ciryl of Jerusalem: catechetical lectures, 4:35&36

“first and second Esdras” በማለት ያስቀመጠው ስላለ ምናልባትም ዕዝራ ካልእንና ዕዝራ ሱቱኤልን ያካትታል። እንዲሁ ደግሞ ከአትናቴዎስ በተለየ እርሱ ባለበት ኢየሩሳሌም አስቴርን ደግሞ ያካትታል። ከሐዲስ ኪዳን ፕሮቴስታንቱም የሚቀበለውን የዮሐንስ ራዕይን በቀኖናው ውስጥ አላካተተውም። ይህ የቄርሎስ ቀኖና ከላይ ለአትናቴዎስ በተናገርነው መልኩ የሚታይ ሲሆን ቄርሎስ ከቀኖናው ውጪ ያሉትን መጽሐፍት ሁለተኛ መጽሐፍት አድርጎ ይናገራል። ይህም ቀጥታ “But let all the rest be put aside in a secondary rank”[93] በማለት ተናግሯልና ነው። ታድያ ግን ይህ አነጋገሩ ቃለ እግዚአብሔርን የማበላለጥ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነበቡትን ከመለየት አንጻር ነው። ከቀኖናው መጽሐፍት ሌላ አታንብቡ ብሎ ቢናገር ስለ መናፍቃኑ መጽሐፍት እያወራ እንጂ ስለሌሎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚካተቱት መጽሐፍት መናገሩ አይደለም። ከቀኖና ውጭ ያሉትን ሁሉ ከሆነማ የዮሐንስ ራዕይንም መነበብ እንደሌለበት እያስጠነቀቀ ነው ልንል ነው። ታድያ ግን ራሱ ቅዱስ ቄርሎስም በphilip schaff NPNF2, 7 index መሰረት ከእነዚህ ከቀኖና ውጪ ካሉ መጽሐፍትም ውስጥ በሥራዎቹ ውስጥ ይጠቅሳል። እንግዲህ ሌላውን አታንቡ ብሎ እርሱ ግን ከማንበብም አልፎ በሥራዎቹ ውስጥ በማካተት ሌላውም እንዲያነብ መልሶ እየጋበዘ ይሆን? ይሄ የሚያሳየው “ሌሎችን አታንብቡ” ሲል የመናፍቃንን መጽሐፍት ብቻ እንደሆነ ነው። እንጂ ለማንበብማ ሉተር እንኳን በጀርመንኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜው ላይ ይነበቡ ብሎ አካቷቸው የለም ወይ?

**ጀሮም እና አውግስጢኖስ፡** ጀሮም አስቀድሞ የመጽሐፍት ቀኖና ላይ ያለው እምነት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተት ያለባቸው 22ቱ መጽሐፍት ብቻ እንደሆኑ ይመስላል።[94] ጀሮም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ላቲን የተረጎመ ሲሆን የተረጎመውም ከዕብራይስጡ ነበር። የእብራይስጡን መጠቀሙም ከሌሎች አባቶች ለየት ያደርገዋል። ታድያ በዚህ ትርጓሜው ላይ ከእብራይስጥ ሲተረጉም አይሁድ በሰዓቱ የማይቀበሏቸውን መጽሐፍት እሱም በማስወጣት ነበር። ይህንንም በማድረጉ በሰዓቱ ከነበረው ሌላ አባት ተቃውሞ ደርሶበት ነበር ይህም አባት አውግስጢኖስ ነው። አውግስጢኖስ ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውንም መጽሐፍት በቀኖናው ውስጥ ያካተተ አባት ሲሆን በካርቴጁም ጉባኤ ላይ የተገኘ ነው። ታድያ ግን በሰዓቱ የአውግስጢኖስ ተቃውሞ የነበረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀባይነት ያለው ሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ ሲሆን ጀሮም ግን ከእብራይስጡ ከመተርጎሙ ጋር ተያይዞ ነው። ምክኒያቱም በግሪኩና በእብራይስጡ መካከል ብዙ ልዩነቶች ነበሩና ሰዎችንም ማደናገር

---

[93] ibid
[94] Jerome, Letter 53:6-8

ስለሚጀምሩ ከሐዋርያት ጀምሮ የተላለፈልንን ትርጓሜ እንቀበል በሚል ነበር። ይህንን ሃሳብ ሁለቱ አባቶች በተላላኩት ደብዳቤ ላይ እና ከደብዳቤው በኋላም አውግስጢኖስ city of God በተሰኘው ሥራው book 18 ላይ በሁሉም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን ያለው ትርጓሜ የእብራይስጡ እንደሆነ ይናገራል። ታድያ ግን በመጽሐፍት ቀኖና ላይም ልዩነት ኖሮ እንዴት ሳይነጋገሩበት የሚለውን ነገር ስንመለከት ምናልባትም ጀሮም በቀኖና ውስጥ ያላካተታቸውንም መጽሐፍት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆኑ ሳያምንባቸው ቀርቶ ሳይሆን አይሁድ ስላልተጠቀሙባቸው ብቻ በሚል ሃሳብ እንደሆነ እንድንመለከት ይጋብዘናል። ታድያ ግን እውን ሌሎቹን መጽሐፍት ቃለ እግዚአብሔር ወይም ደግሞ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሆኑ ለማመኑ ምን ማስረጃ ይኖራል ቢሉ ከላይ በሌሎች አባት ላይ እንዳየነው ጀሮምም ከእነዚህ መጽሐፍት በተደጋጋሚ ጠቅሶ ማስተማሩና ዶክትሪናል ለሆኑ ጉዳዮችም ከሌሎች እርሱ በቀኖናው ውስጥ ካላካተታቸው መጽሐፍት ጋር እያደረገ ተጠቅሞባቸዋልና ነው። ሙሉ ሥራውን ባልያዘው Philip schaff, NPNF2, 6 index ላይ እንደተቀመጠው ወደ 65 ጊዜ ከእነዚህ መጽሐፍት የተጠቀሰ ሲሆን ወደ 55 የሚሆኑት ቀጥታ ከእራሱ ናቸው። ለምሳሌ ጀሮም እንዲህ ይላል፡

“**መጽሐፍ ቅዱስ** “የከበደ ሸክምን አንስተህ በራስህ አትሸከም” **አይልምን?**(ሲራክ 13፡2)[95]

ልንመለከት የሚገባው ሲራክን መጥቀሱን ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ሲጠቅሰው ምክኒያት እንኳን አሳጥቶ “መጽሐፍ ቅዱስ” ብሎ ይጠራዋል። ሌሎችም እንዲሁ ዶክትሪናል ነገሮችን ያስረዳባቸዋል። ከዚህ አንጻር ጀሮም ምናልባት መጽሐፍት ላይ ባለው እምነቱ አድጎ ሊሆንም ይችላል የሚል እምነት አለኝ።

## <u>ሐዲስ ኪዳን</u>

ከዚህ ቀደም እንዳየነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም እንደተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ሐዋርያቱ ይመሩበትና ይማሩበት ዘንድ የሰጣቸው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት አልነበሩም። የጌታም ዋናው ዓላማ ሰዎችን በመጽሐፍት በኩል ማግኘት ሳይሆን ቀጥታ በመንፈሱ በኩል ማግኘት ነውና ለሃዋርያቱ ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራቸው መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ቃል ገባላቸው። ጌታችን ኢየሱስ ካረገ በአስረኛው ቀን በ120ው ቤተሰብ ላይ ያ ቃል የገባላቸውን ቅዱስ መንፈስ አፈሰሰው። ያ ቅዱስ መንፈስ በሕብረት በተቀመጡት ደቀመዛሙርት ላይ በወረደ ጊዜ ደግሞ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

---

[95] To Eustochium, Epistle X(10)

ተመሰረተች። ይህ ሁሉ ሲሆን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት የሉም። በኋላ ዘመን ግን ደቀ መዛሙርት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ደብዳቤዎችን መጻፍ ጀመሩ። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በጽሑፍም ያስተምሩ ጀመር። እነርሱ በሰዓቱ የተለያየ ቦታ ሆነው የጻፏቸው መልእክታትና ወንጌላት በሰዓቱ በነበሩ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ተቀምጦ ይነበብ ነበር። በእነዚህ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ቁጥር ላይ እስከ 4ኛው መቶ ክ/ዘመን ድረስ በተለያዩ አባቶች የተለያየ ምልከታ ነበር። አራቱ ወንጌላት ላይ ምንም ጥያቄ አልነበረም። በእርግጥ በሰዓቱ የነበሩት ኖስቲክ መናፍቃን በቅዱሳን ሐዋርያት ስም እያደርወጉ ወንጌላትን ይጽፉ ነበር። ይህም ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናችን የተለዩ መጽሐፍት ናቸው። መልእክታትና የዮሐንስ ራዕይ ላይ አንዳንዶቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚመድቧቸውም የማይመድቧቸውም ነበሩ። ስለዚህም የቀኖና ጉዳይ ሐዲስ ኪዳን ላይም ሂደታዊ ነበር። ቤተ ክርስቲያን በ4ኛው ክ/ዘመን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት 27 እንደሆኑ ተናገረች። በእርግጥ በተለያዩ ሃገራት ላይ የተለያዩ የሥርዓት መጽሐፍቶችንም የሚያካትቱ ነበሩ። ለምሳሌ እንደ እነ ቀለሜንጦስ እና ሄርማስ ያሉትን ይጨምራሉ። እነዚህ መጽሐፍት ጥንታውያን እደ ክታባት ላይም ከሐዲስ ኪዳን ጋር አብረው ያሉ ናቸው። በእኛ ሃገርም እንዲሁ እነዚህ 27ቱ ቅዱሳት መጽሐፍት ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ስምንት ደግሞ የሥርዓት መጽሐፍት አሉ። በቅዳሴ ላይ ግን የሚነበቡት 27ቱ ብቻ ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ(ቅዳሴ ላይ) የሚነበቡ ቅዱሳት መጽሐፍት ቀኖና ብለን ልንዘረዝር የምንችለው 27ቱን ነው ማለት ነው።

## ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

(ሮሜ 16፡27)

## ዋቢ መጻሕፍት


- ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ
- የኢቶጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000ዓም
- St Jerome: The Principal Works of St. Jerome: Philip schaff, NPNF2 vol. 6
- St Cyril of Jerusalem and Gregory Nazianzen: Philip schaff, NPNF2 vol. 7
- St Athanasius: Select Works and Letters: Philip schaff, NPNF2 vol. 4
- St John Chrysostom: homilies on the gospel of St Mathew
- St Irenaeus: against heresies
- St Epiphanius of Salamis: panarion
- St John Chrysostom: Homilies on 2 Thessalonians
- St Gregory of Nyssa: on “Not three Gods”
- St. Ephrem the Syrian: Hymns on Paradise
- St Cyprian treatises and epistles from ANF vol. 5 by Philip schaff
- Clement of Alexandria: the instructor and Miscellanies from ANF vol.2
- St Clement of Rome: First epistle
- Epistle of barnabas: philip schaff ANF vol. 1
- Justin Martyr: dialogue with trypho: philip schaff ANF vol. 1
- Eusabius, ecclesiastical history: Philip schaff, NPNF2 vol. 2
- Council of carthage: Philip schaf: NPNF2. vol.14
- Fr Tadros Y. Malaty: Tradition and Orthodoxy
- The orthodox study bible
- New Revised Standard Version(NRSV) (English bible)
- Emmanuel tov: textual criticism of the Hebrew bible, 2nd ed.
- The Complete Works of Josephus
- Cohen, Shaye: From The Maccabees to The Mishnah 2nd ed.
- Edersheim, Alfred: The Life and Times of Jesus the Messiah
- F.F. Bruce: The canon of scripture
- The Babylonian Talmud
- Karl Josef von Hefele: A Hstory Of The Councils Of The Church
- EDMON L. GALLAGHER and JOHN D. MEADE: The biblical canon lists From early christianity_texts and analysis
- THE DEAD SEA SCROLLS BIBLE translated by MARTIN ABEGG, JR., PETER FLINT, AND EUGENE ULRICH
- Christian D. Ginsburg: The essenes, their history and doctrines